# አዲስ ዘመን
ኢፕድ
ረቡዕ
83ኛ ዓመት ቁጥር 156 የካቲት 6 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# የሚሠራና የሚተጋ እጅ ሀገር እንደሚቀይር ጅግጅጋ ጥሩ ማሳያ ናት

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የሚሠራና የሚተጋ እጅ ሀገር እንደሚቀይር ጅግጅጋ ከተማ ጥሩ ማሳያ ናት ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ገለጹ። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ሰሞኑን በሶማሌ ክልል የተለያዩ የልማት ስራዎችን ጎብኝተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በወቅቱ፤ ጉብኝቱ ብዙ ትምህርት የተገኘበት መሆኑን ጠቁመው፤ የሚሠራና የሚተጋ እጅ ሀገር እንደሚቀይር ጅግጅጋ ከተማ ጥሩ ማሳያ ናት ብለዋል።

የሚሠራና የሚተጋ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## “የኢትዮጵያን ነፃነት ለመጠበቅ ሾተሉን ወደ አፎቱ መመለስና ቁጣን ወደ ትዕግስት መቀየር ይጠበቅብናል”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን ነጻነት ለመጠበቅ ሾተሉን ወደ አፎቱ መመለስና ቁጣን ወደ ትዕግስት መቀየር ይጠበቅብናል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የዓድዋ ድል መታሰቢያ የምረቃ መርሀ ግብር ላይ ባስተላለፉት መልዕክት፤ የኢትዮጵያን ነጻነት

“የኢትዮጵያን ነፃነት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ወይዘሮ መሰረት ዳምጤ

## በበጀት ዓመቱ 162 ተቋማትና 54 ቅርንጫፎቻቸው ኦዲት ተደርገዋል

- 5 ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ርምጃ ተወስዷል
- 150 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ገንዘብ ማስመለስ ተችሏል

ገጽ 4

# “የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ለሰላም ቅድሚያ የሚሰጥ በመሆኑ ለሌሎች ሀገራት ተምሳሌት ነው”

- የዲፕሎማሲ ሳምንት አውደ ርዕይን የጎበኙ ቻይናውያን ጥንዶች

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ለሰላም ቅድሚያ የሚሰጥ በመሆኑ ለሌሎች ሀገራት ተምሳሌት ሊሆን እንደሚችል መገንዘባቸውን የዲፕሎማሲ ሳምንት አውደ ርዕይን የጎበኙ ቻይናውያን ጥንዶች ገለጹ፡፡

“ዲፕሎማሲያችን ለብሔራዊ ጥቅማችን” በሚል መሪ ሃሳብ በሳይንስ ሙዚየም የተዘጋጀውን የዲፕሎማሲ ሳምንት አውደርዕይ ኢትዮጵያዊያንን ጨምሮ የተለያዩ ሀገራት ዜጎች እየጎበኙ ይገኛሉ።

አውደ ርእዩን ሲጎበኙ ያገኘናቸው ቻይናውያን ጥንዶች ሄሌን ዢ እና ባለቤታቸው ዌን ቲያን በአውደ ርእዩ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ አካሄድ ከቀደምት የነገሥታት ጊዜ ጀምሮ ለሰላም ቅድሚያ የሚሰጥ መሆኑን እንደ ተገነዘቡ ገልጸው ለሌሎች ሀገራት ተምሳሌት ሊሆን

“የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ሄሌን ዢ


ዌን ቲያን

ፎቶ - ሀዲስ አብርሃ




ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA
የዜጎች ጤና ለሃገር ብልጽግና!
HEALTHIER CITIZENS FOR PROSPEROUS NATION!

# ሚኒስቴሩ የተለያዩ ድጋፎችን ለጤና ተቋማት አበረከተ

- ከ700 በላይ አምቡላንሶች ግዢ ተፈጽሟል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- የጤና ሚኒስቴር የተለያየ ወጪ የተደረገባቸውን 168 ተሽከርካሪዎችና ከ450 በላይ ኮምፒውተሮችን ለፌዴራል ጤና ተቋማትና ለጤና ቢሮዎች በድጋፍ መልክ አበረከተ።

ጤና ሚኒስቴር ከዓለም ባንክ ጋር በመተባበር ከ700 በላይ አምቡላንሶችን ግዢ መፈጸሙ ተመላክቷል፡፡

ጤና ሚኒስቴር ከዓለም ባንክና ከተጠሪ ተቋማት በገኘው ድጋፍ የተገዙ ተሽከርካሪዎችንና ኮምፒውተሮችን ለፌዴራል የጤና ተቋማትና ለክልል ጤና ቢሮዎች ትናንት ሲያስረክብ የጤና ሚኒስትር ዴኤታ ደረጀ ድጉማ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ ድጋፉ የጤና ተቋማትን አገልግሎት ለማሻሻል ወሳኝነት አለው።

የጤና ተቋማት የሕክምና ቁሳቁሶችንና ሕመምተኞችን የሚያጓጉዙበት ተሽከርካሪ እንዲሁም የጤና መረጃ ሥርዓትን በአግባቡ የሚይዙበት ኮምፒውተሮች ማግኘታቸው አገልግሎታቸውን እንዲያሳድጉ ይረዳል ብለዋል።

ለ160 ተሽከርካሪዎቹ ግዥ የዓለም ባንክ የገንዘብ ድጋፍ ማድረጉን ጠቁመው፤ የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣንና የጤና ሚኒስቴር በበኩላቸው 450 የላፕቶፕ ኮምፒውተሮቹን መግዛታቸውን አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በበኩሉ ስምንት የላቦራቶሪ ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎችን ድጋፍ ማድረጉንም ገልጸዋል።

ከ160 ተሽከርካሪዎቹ ውስጥ 129ኙ ተሽከርካሪዎች ለክልልና ለከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮዎች የሚተላለፉ መሆኑን አስረድተው፤ 31ዱ ተሽከርካሪዎች ደግሞ ለተጠሪ ተቋማት የሚሰጡ መሆናቸውን ተናግረዋል። ድጋፉ ለሁሉም ክልሎችና ለከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮዎች የሚዳረስ መሆኑን አስታውቀዋል።

በሚቀጥሉት ሶስት ዓመት የሚተገበረውን የመካከለኛ ዘመን የልማትና የኢንቨስትመንት እቅድ ለማሳካት የግብዓት አቅርቦት ወሳኝ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የተለያዩ ግብዓቶችን ለክልልና ለከተማ አስተዳደር ጤና ተቋማት ድጋፍ የማድረግ ሥራው ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል፡፡

በቀጣይ ከዓለም ባንክ ጋር በመተባበር ከ700 በላይ አምቡላንሶች ግዢ መፈጸሙን አመላክተው፤ ወደሀገር ሲገቡ ለተለያዩ የጤና ተቋማት ይሰራጫሉ ብለዋል፡፡

ድጋፍ የተደረገላቸው ተቋማት ግብዓቶቹን ለታለመለት ዓላማ በማዋል በአግባቡ እንዲጠቀሙት ሚኒስትር ዴኤታው፤ አሳስበዋል፡፡

ድጋፉን የተረከቡት የጤና ቢሮ ኃላፊዎች ለተደረገላቸው ድጋፍ አመስግነው፤ የታለመለት ዓላማ ላይ እንደሚያውሉት ቃል ገብተዋል።

# የኢትዮጵያ ፓርላማ ከጀርመን አቻው ጋር ያለውን ግንኙነት አጠናክሮ ይቀጥላል

**መስከረም ሰይፉ**



አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ፓርላማ ከጀርመን አቻው ጋር ያለውን ግንኙነት አጠናክሮ እንደሚቀጥል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የውጭ ግንኙነትና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አስታወቀ።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውጭ ግንኙነትና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና የጀርመን የፓርላማ አባላት በሁለቱ ሀገራት ግንኙነት ዙሪያ በትናንትናው እለት ውይይት አካሂደዋል።

የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታን ለጀርመን የፓርላማ አባላት ያስረዱት የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ ፈትሂ ማህዲ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያና ጀርመን ከመቶ ዓመታት በላይ የዘለቀ ግንኙነት ያላቸው ሲሆን፤ የሁለቱ ሀገራት የፓርላማ አባላቶችም በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በጋራ ሠርተዋል።

በሁለቱ ሀገራት መካከል ከ80 በላይ ስምምነቶች መኖሩን የጠቀሱት ምክትል ሰብሳቢው፤ የንግድ ግንኙነታቸውም ጥሩ የሚባል መሆኑን አመላክተዋል።

ኢትዮጵያ ወደ ውጭ ከምትልከው ቡና፣ አበባ እንዲሁም የቆዳ ምርቶች አብዛኛው ገዢ ሀገር ጀርመን ስትሆን ኢትዮጵያም መድኃኒቶችን ፣ኬሚካሎችን እንዲሁም ማሽኖች ከጀርመን እንደምታስገባ ተናግረዋል። ይህም ያላቸውን ግንኙነት እንደሚያሳይና ይህንን ግንኙነት ማጠናከር እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ካላት ሕዝብ ብዛትና እያደገ ካለ ኢኮኖሚ አንጻር አንድ ወደብ ብቻ ስትጠቀም መቆየቷ በርካታ ኢኮኖሚያዊ ችግር እየፈጠረ በመሆኑ ከሶማሊላንድ ጋር የወደብ ስምምነት መፈጸሟንም አስረድተዋል።

ኢትዮጵያ የባህር በሩን ለልማት አላማ ብቻ እንደምትፈልገውና ይህም የሚሆነው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን በማይጥስና ሌሎች ሀገራትን በማይጎዳ መልክ መሆኑን በውይይቱ ላይ አንስተዋል።

ምክትል ሰብሳቢው ኢትዮጵያ ከፕሪቶሪያው ስምምነት በኋላ በርካታ ሥራዎች መሥራቷን የተናገሩ ሲሆን፤ ትግራይ ክልልን መልሶ ከማቋቋም አንጻር በመብራት፣ በውሃ፣ በቴሌኮም እንዲሁም የአየር ትራንስፖርትን ከመመለስ አኳያ የኢትዮጵያ መንግሥት በርካታ ሥራዎች ማከናወኑን አንስተዋል።

የጀርመን ፓርላማ ቡድን መሪ ሞኒካ ግሩተርስ (ፕ/ር) በበኩላቸው፤ ከምክር ቤቱ ጋር በጋራ ለመሥራት የሚደረገው ጥረት እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለማሳደግ የግብርና ዘርፉን ማዘመን እንደሚገባ ገልጸው፤ በቀጣይ ሀገሪቱ በምታደርገው የግብርና እንቅስቃሴ ላይ የግብርና ምርትን ለማሻሻል ቴክኖሎጂን መጠቀም እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

ፕሮፌሰር ሞኒካ በኢትዮጵያና በሶማሌ ላንድ መካከል የተደረገው የባህር በር ስምምነት ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን በማይጥስ ሁኔታና ከጎረቤት ሀገራት ጋር በመወያየትና በመግባባት መሥራት እንደሚያስፈልግ ተናግረው፤ ጀርመን ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ዘርፈ ብዙ ግንኙነት አጠናክራ እንደምትቀጥል አመላክተዋል።



# የባህር በር ስምምነቱ የቀጣናውን ሀገራት የኢኮኖሚ ትስስር ማጠናከር የሚያስችል ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የባህር በር ስምምነቱ የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ሀገራትን የኢኮኖሚ ትስስርን በማጠናከር ዕድገታቸውን በፈጣን ሁኔታ ማሳደግ የሚያስችል ነው ሲሉ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስ መምህር ረዳት ፕሮፌሰር ሽመልስ ኃይሉ ገለጹ፡፡

መምህር ሽመልስ ኃይሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ሀገራት በወደብ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ኢኮኖሚያዊ ትስስራቸውን ካጠናከሩ የተሻለ ዕድገት ማስመዝገብ ይችላሉ።

በቀጣናው ያለውን ሀብት ይበልጥ ለመጠቀም ሀገራቱ የተሻለ ትስስር መፍጠር ይገባቸዋል ያሉት መምህሩ፤ ከጦርነት ይልቅ በጋራ የመልማት ልምድን በማዳበት የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራትን የተሻለ መጥቀም የሚቻልበት ሰፊ አማራጭ መኖሩን ጠቁመዋል።

የባህር በር ለኢትዮጵያ ቅንጦት ሳይሆን የሀገርን ሉዓላዊነት፣ ኢኮኖሚ፣ ደህንነትና ወታደራዊ እንቅስቃሴን የሚወስን በመሆኑ ለነገ የሚተው ጉዳይ እንዳልሆነ አንስተዋል።

ቀይ ባህርና የኤደን ባህረ ሰላጤ የዓለም የኢኮኖሚ፣ ደህንነትና የፖለቲካ እንቅስቃሴን የሚወስን ቀጣና መሆኑን ጠቁመው፤ በአካባቢው ኢትዮጵያ የባህር በር እንዲኖራትመፈለጓ ወሳኙ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ መሆኑን ተናግረዋል።

የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት በቀይ ባህር ዙሪያ ያለማ ሰፊ መሬት እንዳላቸው ገልጸው፤ ኢትዮጵያን የጋራ ተጠቃሚ በሚያጎለብት መልኩ ኢኮኖሚዋን ለማሳደግ ከቀጣናው ሀገራት ጋር በባህር በር ጉዳዮች በጋራ መሥራቷን መቀጠል እንዳለባት አመላክተዋል።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ 120 ሚሊዮን በላይ ሕዝብን የያዘ መሆኑን የገለጹት መምህሩ፤ ከሱማሊ ላንድ ጋር የተደረሰው የመግባቢያ ስምምነት ለኢትዮጵያ አንድ ጥሩ እፎይታና ኢኮኖሚዋን ወደ ጥሩ መንገድ የሚወስድ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በአፍሪካ ቀንድ ከኢትዮጵያና ደቡብ ሱዳን ውጪ ያሉ ሀገራት የባህር በር እንዳላቸው ገልጸው፤ ኢትዮጵያ አንድ ወደብና ኮሪደር ላይ ብቻ መንጠልጠል እንደሌለባት የሚገልጹት መምህር ሽመልስ፤ በቀጣናው አማራጮችን መጠቀም ኢኮኖሚያዊ ትስስርን የሚፈጥር መሆኑንም አመላክተዋል።

ኢትዮጵያ አንድ ወደብና ኮሪደር ላይ ብቻ መንጠልጠል እንደሌለባት የተናገሩት መምህር ሽመልስ፤ በቀጣናው አማራጮችን መጠቀም ኢኮኖሚያዊ ትስስርን የሚፈጥር መሆኑንም አስረድተዋል።

ሱዳን ፣ኬንያ፣ ሱማሊያ፣ ጂቡቲ፣ ኤርትራና ሱማሊያ ለኢትዮጵያም አማራጭ የወደብ መዳረሻ መሆን የሚችሉ ሀገራት መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

ኢትዮጵያ ያቀረበችው የባህርበር ጥያቄ ከሁሉም ሀገራት ጋር ለመስማማት የሚያስችል መሆኑን ጠቅሰው፤ በአፍሪካ ቀንድ የንግድ ትስስሩን በማሳደግ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን የሚያጎለብት ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት በአፍሪካ ቀንድ፣ በቀይ ባህርና በሕንድ ውቅያኖስ አካባቢ በሚደረገው እንቅስቃሴ የሚወሰን መሆኑን ጠቅሰው፤ የባህርበር የወደፊት ኢትዮጵያን አቅም የሚለውጥና አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

በመጨረሻም እንደሀገር የውስጥ ችግሮችን መፍታት ፣ብሔራዊ ጥቅም ላይ መግባባት እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፤ የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ጋር በዲፕሎማሲያዊ መንገድ መነጋገርና ማሳመን እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያዊያን ውስጣዊ አንድነት የውጪ ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ ጥንካሬን የሚያመጣ መሆኑን ተናግረው፤ በሀገሪቱ ቀጣይ እጣ ፋንታ ላይ መግባባት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን መፍጠር ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

# የሰቆጣ ቃልኪዳንን በ700 ወረዳዎች ለማስፋፋት የሚረዳ የሀብት ማሰባሰቢያ ዕቅድ ይፋ ሆነ

**አስናቀ ፀጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የሰቆጣ ቃልኪዳንን በ700 ወረዳዎች ላይ ለማስፋፋት የሚረዳ የሀብት ማሰባሰቢያ ዕቅድ ይፋ መሆኑን የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የሰቆጣ ቃልኪዳን የሀብት ማሰባሰቢያ ዕቅድ ትናንት ይፋ በተደረገበት ወቅት የማስፋፊያ ምዕራፍ ትግበራው በድምሩ 146 ቢሊዮን ብር ወጪ እንደሚጠይቅ ተገልጿል።

በወቅቱ የጤና ሚኒስትር ዴኤታ ደረጀ ዱጉማ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ ከአንድ ወር በፊት የሰቆጣ ቃልኪዳንን ከ240 ወደ 700 ወረዳዎች ለማስፋት ውሳኔ ተላልፏል፡፡ ውሳኔውን ተከትሎ ለቃልኪዳኑ ማስፋፊያ የሚውል ዝርዝር የሀብት ማሰባሰብ ዕቅድ ይፋ መደረጉን አስረድተዋል፡፡

የሰቆጣ ቃልኪዳን በየአምስት ዓመቱ በሦስት ዙር ወደ ሥራ የሚገባ መሆኑን ጠቁመው፤ በመጀመሪያው ዙር በ240 ወረዳዎች ላይ ተግባራዊ ሲሆን መቆየቱን አስታውሰዋል።

አሁን ላይ በሁለተኛው ዙር በ700 ወረዳዎች ላይ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን አብራርተው፤ የሳብት ማሰባሰቢያ ዕቅዱ የተሻለ ለመንቀሳቀስ ይረዳል ብለዋል።

በፌዴራል፣ በክልል መንግሥታትና በአጋር ድርጅቶች በየዓመቱ ለሥርዓተ- ምግብ ማሻሻያ ሥራዎች 12 ቢሊዮን ብር ወጪ እንዲያደርጉ ታስቦ ወደ ሥራ መገባቱን የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የፌዴራልም ሆነ የክልል መንግሥታት እንዲሁም ሁሉም አጋር ድርጅቶች በገቡት ቃልና መሠረት ለማስፋፊያው የሚውለውን በጀት እንዲያቀርቡ ውይይት እየተካሄደ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በመጀመሪያዎቹ አምስት ዓመታት ላይ በሰቆጣ ቃልኪዳን ትግበራ አበረታች ውጤት በመገኘቱ በተጨማሪ 700 ወረዳዎች ላይ ሥራውን ለማስፋት ማስፈለጉን አስረድተዋል።

እ.ኤ.አ በ2022 በተሠራ ዓለም አቀፍ ጥናት ቀደም አጋር ድርጅቶችም ገንዘብ አሰባስበው ሰፊ ሥራ በመሥራታቸው ከ99 ሺ በላይ የሚሆኑ ሕፃናትን ከመቀንጨር ነፃ ማድረግና ከሦስት ሺህ በላይ የሚሆኑ ሕፃናትን ከሞት መታደግ መቻሉ ቃልኪዳኑን በተጨማሪ ወረዳዎች ላይ ለማስፋፋት ምክንያት መሆኑን አብራርተዋል፡፡

በተመጣጠነ የምግብ እጥረት ምክንያት የሚከሰተውን የመቀንጨር ምጣኔ ከመቀነስ አኳያ ከ20 ዓመት በፊት የነበረውን 58 ከመቶ የመቀንጨር ችግር በአሁኑ ጊዜ ወደ 39 ከመቶ ዝቅ ማድረግ መቻሉንም ሚኒስትር ዴኤታው ገልጸዋል፡፡

በተመሳሳይ አጣዳፊ የምግብ እጥረት ችግርን ለመቅረፍ የሰቆጣ ቃልኪዳን አብዛኛዎቹን አጋር ድርጅቶችን የሚያሰባስብና ይበልጥ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሠራበት የሚያደርግ በመሆኑ ውጤቱን በሌሎች ወረዳዎች ለማስፋፋት የሀብት ማሰባሰቢያ ዕቅድ መዘጋጀቱን ተናግረዋል፡፡

ሆኖም ባለፉት አምስት ዓመታት በሀገሪቱ በነበሩ የተለያዩ የፀጥታና ሌሎችም ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ችግሮች ምክንያት የመቀንጨር ችግር በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ተመልሶ መጨመሩን አስታውቀዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ያለውን የመቀንጨር ምጣኔ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለመቀነስ ተጨማሪ ሥራ መስራት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፡፡

የተመጣጠነ ምግብ እጥረት በኢትዮጵያ ትልቅ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የማህረሰብ ጤና ችግር መሆኑን ተከትሎ ችግሩን ለመፍታት የሰቆጣ ቃልኪዳን በ2007 ዓ.ም ይፋ መደረጉ የሚታወስ ነው። የፌዴራል መንግሥትም እ.ኤ.አ በ2030 ከሁለት ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናትን የመቀንጨር ችግር ለመቅረፍ አልሞ እየሠራ ይገኛል።



**ደረጀ ዱጉማ (ዶ/ር)**



# ከክልሉ የቱሪዝም ዘርፍ በግማሽ ዓመቱ 25 ቢሊዮን ብር ገቢ ተገኘ

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- ከክልሉ የቱሪዝም ዘርፍ በግማሽ ዓመቱ 25 ቢሊዮን ብር ገቢ መገኘቱን የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን አስታወቀ።

የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ነጋ ወዳጆ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥም በክልሉ ያሉ የቱሪዝም መዳረሻዎችን አገልግሎት አሰጣጥ በማዘመን እንዲሁም መስህቦችን በማስተዋወቅ ክልሉን ለጎብኚዎች ምቹና ተመራጭ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል።

በግማሽ ዓመቱ ከስምንት ሚሊዮን በላይ የሀገር ውስጥና 139 ሺህ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ክልሉን መጎብኘታቸውን ጠቁመው፤ በዚህም 25 ቢሊዮን ብር ገቢ መገኘቱን አመላክተዋል።

ክልሉን ከጎበኙት መካከል በመንፈሳዊ ጉዞዎች ፣ በስብሰባዎች እንዲሁም በተለያዩ የአደባባይ በዓላትና በጉብኝት መልክ ወደ ኦሮሚያ የተጓዙ ሰዎች መኖራቸውን አብራርተዋል።

በኦሮሚያ ክልል በቱሪዝም ዘርፍ ወደ ገቢ ምንጭነት ሊቀየሩ የሚችሉ በርካታ መስህቦች መኖራቸውን አቶ ነጋ ገልጸው፤ ባለፉት ሦስት ዓመታትም እነዚህን መስህቦች በማልማት ዘርፉን የማነቃቃት ሥራ ሲሠራ ቆይቷል ብለዋል።

የቱሪዝሙ ዘርፍ የተለያዩ አገልግሎት ሰጪዎች ገቢያቸው እንዲያድግ በማገዝ ረገድ አዎንታዊ ሚና እንዳለው ተናግረው፤ ክልሉ በቀጣይ ስድስት ወራት ውስጥ የተሻለ ገቢ እንዲገኝ እየሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

በክልሉ የተለያዩ የጉብኝት መርሀ-ግብሮች መኖራቸውን የገለጹት ኮሚሽነሩ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የእግር ጉዞ የሚያደርጉ ማህበራት በስፋት ኦሮሚያን እየጎበኙ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ኮሚሽኑ የውጭ ሀገር ዜጋ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያውያንም ክልሉን እንዲጎበኙ የማስተዋወቅ ሥራ እየሠራ መሆኑን ተናግረው፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህም የሀገር ውስጥ ጉብኚዎች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱን ገልጸዋል።

ወደክልሉ የቱሪዝም መዳረሻ ቦታዎች ለመጓዝ የሚያስችል በቂ መሠረት ባይኖርም በዋና ከተሞች አካባቢ ያሉ መሠረተ ልማቶች ጥሩ የሚባሉ በመሆናቸው ከከተማ ራቅ ብለው ወደሚገኙ አካባቢዎች በርካታ መሠረተ ልማቶች እየተሠሩ መሆኑ ለቱሪዝም ዘርፉ ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴ አለ ብለዋል።

በክልሉ የሀይቆች፣ የአዕዋፋት፣ የተፈጥሮ መስህቦችና የኮንፈረንስ እንዲሁም የተለያዩ የቱሪዝም ዓይነቶችን ሳቢና ለጎብኚዎች ምቹ ለማድረግ በትኩረት እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

# የአፈር ማዳበሪያ በጊዜ እንዲዳረስ ሚኒስቴሩ ጥብቅ ክትትል እንዲያደርግ ቋሚ ኮሚቴው አሳሰበ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የአፈር ማዳበሪያ በተለይም ለመኸር አብቃይ አካባቢ አርሶ አደሮች በጊዜና በፍትሐዊነት እንዲሰራጭ ግብርና ሚኒስቴር ጥብቅ ክትትል እና ቁጥጥር እንዲያደርግ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰበ፡፡

ቋሚ ኮሚቴው የግብርና ሚኒስቴር እና የተጠሪ ተቋማቱን የስድስት ወራት አፈጻጸም በገመገመበት ወቅት የአፈር ማዳበሪያ በጊዜ እንዲገዛ ውሳኔ በማሳለፍ አምና የነበረውን ጫና ለማረም የተሠራውን ሥራ በበጎነት ተመልክቷል፡፡

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ሰለሞን ላሌ የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት ለአርሶ አደሮች ማድረስ ኃላፊነቱ የክልሎች ቢሆንም ሥራው ለክልሎቹ ብቻ ሊተው አይገባም፣ ሚኒስቴሩ ጥብቅ ክትትልና ለበልግ አብቃይ አካባቢዎችም ቶሎ እንዲዳረስ ትኩረት እንዲሰጥ አሳስበዋል፡፡

በማዳበሪያ ስርጭት ሕገ ወጦች ዕድል እንዳያገኙ መደረግ እንዳለበት የተናገሩት አቶ ሰለሞን፣ የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኙ ምርቶች ወጪ ንግድ አፈጻጸምን ለማሻሻል ትኩረት እንዲደረግና የጸጥታ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ግብአት በጊዜ እንዲደርስ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር እንዲሠራም አሳስበዋል፡፡

የግብርና ሚኒስትሩ ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) ባቀረቡት ሪፖርት፤ ባለፈው ምርት ዘመን በተለይም መኸር ላይ የተስተዋለውን የአፈር ማዳበሪያ የአቅርቦት ችግር ለመፍታት በተደረገው ሪፎርም ማዳበሪያ በወቅቱና በተሻለ ዋጋ መግዛት መቻሉን ጠቁመዋል፡፡

ዘንድሮ ለማዳበሪያ ግዢ በተመደበው 71 ቢሊዮን ብር አንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን ቶን (19 ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል) ማዳበሪያ መግዛት መቻሉን አንስተዋል፡፡ 2016/17 ፍላጎት ሁለት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ቶን ወይንም 23 ሚሊዮን ኩንታል ግዥ ለመፈጸም እቅድ እንደነበረና ዘንድሮ ለማዳበሪያ ግዢ የተመደው አምና ከተገዛው ጋር የስድስት ሚሊዮን ኩንታል ብልጫ እንዳለውም አንስተዋል፡፡

አምና የተመደበልን አንድ ቢሊዮን እና የትግራይን ጨምሮ 59 ቢሊዮን ዶላር 12 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ግዢ መፈጸሙን አስታውሰዋል፡፡

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ አምና 12 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ለመግዛት መንግሥት ድጎማ አድርጎ የነበረው 21 ቢሊዮን ብር ሲሆን፤ ዘንድሮ 19 ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል ተገዝቶ ድጎማ የተደረገው 16 ቢሊዮን ብር ብቻ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡



**አቶ ሰለሞን ላሌ**

በአፈር ማዳበሪያ ግዢ የመንግሥትን የድጎማ ጫና በመቀነስ በማዳበሪያ ግዢ ውስጥ 20 ቢሊዮን ብር ማዳን መቻሉን ጠቁመዋል፡፡

ከተፈጸመው 19 ነጥብ አራት ሜትሪክ ቶን የማዳበሪያ ግዢ ጂቡቲ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ መድረሱን፣ ሰባት ሚሊዮን ኩንታል መጫኑን በአመት ከሚያስፈልገው ውስጥ 36 ነጥብ ስምንት በመቶ ሀገር ውስጥ መግባቱን ጠቁመዋል፡፡

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ የበልግና የመስኖን እርሻ ሊሸፍን የሚችል ማዳበሪያ ሀገር ውስጥ ገብቷል፡፡ በተያዘው ፍጥነት ከቀጠለ ዘንድሮ የማጓጓዝ ሥራው ግንቦት ወር ላይ ይጠናቀቃል፡፡ በቀን 150 ሺህ ኩንታል ማዳበሪያ እየተጫነ ይገኛል፡፡

አማራ ክልልና ተመሳሳይ ትኩረት የሚሹ አካባቢዎችም በጸጥታ ችግር ምክንያት ማቅረብ በሚገባን ያክል ግብአት ለማቅረብ አልቻልንም፡፡ ከሚመለከታቸው ጋር ንግግር ተደርጓል ብለዋል፡፡

ባለፉት ስድስት ወራት ግብርናው ከወጪ ንግድ አንድ ነጥብ ሦስት አምስት ቢሊዮን ዶላር ማስገባቱንም አመልክተዋል፡፡

የወጪ ንግዶች ካለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በመጠን 10 በመቶ ጭማሪ ሲያሳይ፤ በገቢ 195 ሚሊዮን ዶላር ቅናሽ ማሳየቱን ከእቅዱ አንጻር ጉድለቶች እንዳሳየ ተናግረዋል፡፡ የማካካሻ ሥራ እንደሚተገበርም አመልክተዋል፡፡

በዘር አቅርቦት ባለፉት ሦስት ዓመታት በየዓመቱ አንድ ሚሊዮን ኩንታል የነበረውን ወደ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል ለማሳደግ መታቀዱን፣ ዘንድሮ ወደ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ለማሳደግ ትኩረት መደረጉንም ተናግረዋል፡፡

# በበጀት ዓመቱ 162 ተቋማትና 54 ቅርንጫፎቻቸው ኦዲት ተደርገዋል

- አምስት ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ርምጃ ተወስዷል
- 150 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ገንዘብ ማስመለስ ተችሏል

መርድ ክፍሉ


ወይዘሮ መሰረት ዳምጤ

አዳማ፡- በ2015/16 በጀት ዓመት 162 መሥሪያ ቤቶች እና 54 ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቻቸው ላይ የሒሳብ ኦዲት ማድረጉን የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት አስታወቀ። መሥሪያ ቤቱ ባደረገው የኦዲት ሥራ አምስት ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ርምጃ መወሰዱንና በኦዲት ሥራው ያለአግባብ ወጪ የሆነ 150 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ገንዘብ ወደ መንግሥት ካዝና እንዲመለስ መደረጉ ተመላክቷል።

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ዋና ኦዲተር ወይዘሮ መሰረት ዳምጤ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በ2015/16 በጀት ዓመት መሥሪያ ቤቱ 173 መሥሪያ ቤቶችንና 58 ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶችን ኦዲት ለማድረግ አቅዶ ነበር።

በአስራ አንድ መሥሪያ ቤቶችና በአራት ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በጸጥታ ምክንያት ኦዲት ማድረግ አለመቻሉን ጠቁመው፤ በተቀሩት 162 መሥሪያ ቤቶችና 54 ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ላይ የኦዲት ሥራው መከናወኑን አስረድተዋል።

እንደ ዋና ኦዲተሯ ገለጻ፤ የክዋኔ ኦዲትን በተመለከተም በበጀት ዓመቱ 32 አዳዲስ የክዋኔ ኦዲቶችና 12 የክትትል ኦዲቶች ተከናውነዋል።

በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ በሚመለከታቸው አካላት የተጠየቁ 13 ያህል ልዩ ኦዲቶችን ማከናወን እንደተቻለ ጠቁመው፤ ለክልሎች የሚሰጠውን ድጋፍና ድጎማ ኦዲት በተመለከተ 321 ተከታታይ፣ 24 ማረጋገጫና አንድ ዓመታዊ በድምሩ 346 ኦዲቶች መከናወናቸውን አመላክተዋል።

መሥሪያ ቤቱ በሀገሪቱ በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ባደረገው የኦዲት ሥራ በጋምቤላ፣ በወላይታ ሶዶ፣ በቡሌ ሆራ፣ ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲዎች ላይ የኦዲት ክፍተት መገኘቱን ጠቅሰዋል።

በዩኒቨርሲቲዎቹ የሚገኙትን አመራሮች ከኃላፊነት የማንሳት ሥራ መከናወኑንና በተለይ በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ሙሉ የማኔጅመንት አባላቱ ከኃላፊነት እንዲነሱ መደረጉን አብራርተዋል።

በኦዲት ሥራው ከጥቂት ጉድለት በስተቀር ጥሩ አፈጻጸም የነበራቸው ሀዋሳ፣ ቦንጋ፣አዳማ እና ኮተቤ ዩኒቨርሲቲዎች መሆናቸውን ተናግረው፤ ይህም ትምህርት ሚኒስቴር ዩኒቨርሲቲዎችን ሲገመግም የኦዲት ሥራው ላይ ትኩረት መስጠቱ ዋነኛ ምክንያት መሆኑን አመልክተዋል።

በሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ከኦሮሚያ ክልል ደንቢዶሎ፣ ከቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ደግሞ የባህርዳርና የኮምቦልቻ ገቢዎች ቢሮዎች በፀጥታ ችግር ምክንያት የኦዲት ሥራ እንዳልተከናወነባቸው ጠቅሰዋል። በቀጣይ ትግራይ ክልል የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎችን ኦዲት የማድረግ ሥራው ቅድሚያ እንደሚሰጠው ገልጸዋል።

በመሥሪያ ቤቱ የዕቅድና በጀት ዳይሬክተር አቶ ደጀኔ ደቦጭ በበኩላቸው፤ በኦዲት ሥራዎቹ በርካታ ጉድለቶችና ያለአግባብ የወጡ ሂሳቦች እንደሚገኙ አስታውቀዋል።

ኦዲት የሚደረጉ መሥሪያ ቤቶች ለመንግሥት ተመላሽ መሆን ያለበትን ገንዘብ እንዲያሳውቁ በተጠየቀው መሠረት በተለያዩ ተቋማት አንድ ሚሊዮን 535 ሺህ ብር በላይ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣ አንድ ቢሊዮን 235 ሚሊዮን 710 ሺህ ብር በላይ ከደንብና መመሪያ ውጪ የተከፈለ በድምሩ አንድ ቢሊዮን 237 ሚሊዮን 245 ሺህ ብር በላይ እንዲሁም 24 ሺ 390 የአሜሪካን ዶላር በኦዲቱ መገኘቱን አስረድተዋል።

በተለያዩ ተቋማት በተከናወነው የኦዲት ግኝት መሠረት በጥሬ ገንዘብ ጉድለት የተገኘው 21 ሺ 749 ነጥብ 56 ብር፣ ከደንብና መመሪያ ውጪ ከተከፈለው ውስጥ 149 ሚሊዮን 968 ሺህ ብር በጠቅላላ ድምሩ 149 ሚሊዮን 990 ሺህ 661 ብር በላዩ ወደ መንግሥት ካዝና እንዲመለስና የእርምት ርምጃ እንዲወሰድ መደረጉን አመልክተዋል።

## “የኢትዮጵያን ነፃነት ለመጠበቅ ሾተሉን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለመጠበቅ ሾተሉን ወደ አፎቱ መመለስና ቁጣን ወደ ትዕግስት መቀየር ይጠበቅብናል ብለዋል።

አባቶቻችን በሀገርና በመንግሥት መካከል ያለውን ልዩነት ጠንቅቀው እንደሚያውቁ ጠቅሰው፤ በምን መተባበርና መወዳደር እንዲሁም መደጋገፍ፣ መነቃቀፍ እንዳለባቸው ያውቃሉ ሲሉ ገልጸዋል።

እንደ ባልቻ አባ ነፍሶ ሀገርና መንግሥትን ለይተው የሚያውቁ እንደሚያስፈልጉ ገልጸው፤ “አሁን ያለው መንግሥት ላይመች ይችላል፤ ነገር ግን ኢትዮጵያ ሁሌም ትመቻለች” ብለዋል።

ኢትዮጵያ ከዓድዋ እስከዛሬ የፈተናዎቿ ምንጮች ባዳዎችና ባንዳዎች መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ባዳና ባንዳዎች ትናንት በዓድዋ፤ ዛሬም የብልጽግና ጉዞ ላይ የኢትዮጵያ ፈተናዎች መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ባዳዎች መጀመሪያ ፈልፍለው የሚያገኙት ባንዳዎችን ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ባዳዎች የሚወሩን ዝም ብለው መጥተው ሳይሆን ባንዳዎችን ይዘው ነው ብለዋል። “ባዳዎች የሚያቆሙን አይደለም፤ የአባቶቻችን ልጆች ነን” ሲሉም ገልጸዋል።

አባቶቻችን በዓድዋ ደምተውና ሞተው ኢትዮጵያን ነጻ የጥቁር ሕዝቦች ምልክት ማድረጋቸውን ጠቅሰው፤ ከነጻነት ባሻገር ኢትዮጵያን በቴክኖሎጂ ጭምር ለማሳደግ ትልቅ ህልም ይዘው መሥራታቸውን ገልጸዋል።

አባቶቻችን ዋጋ የከፈሉበት ነጻነትና ክብር እሴት ሲሆን፤ ነጻነትና ክብርን ለመቀናጀት የሄዱበት መንገድ ግን እሳት መሆኑን በመግለጽ፤ ልንወርስ የሚገባው ነጻነቱን፣ ክብሩንና አንድነቱን እንጂ እሳቱን መውረስ አይጠበቅብንም ሲሉ አስረድተዋል።

እምቢ ማለት ለወራሪና ለድህነት፣ ለልመና እንዲሁም ለውጫዊ እሳቤ መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህንን ነጻነትና ክብር የወረሰ ኢትዮጵያዊ ዛሬም የምግብ ሉአላዊነትን ለማረጋገጥ የሚተጋ መሆን አለበት ብለዋል።

የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሌሎች የጥቁር ሕዝቦች ሀገራት ሊሠሩት ይችላሉ ያሉት ዶክተር ዐቢይ፤ ነገር ግን የምኒልክ ልጅ፣ የባልቻ ልጅ፣ የገበየሁ ልጅ፣ የአሉላ አባ ነጋ ልጅ መሆን ግን አይችሉም ብለዋል።

የዓድዋ ድል መታሰቢያ ኢትዮጵያውያን በመሆን ታድለን የመሥራት ልቦናና ጥረት ታክሎበት መሠራቱን ጠቅሰው፤ ከ128 ዓመታት በኋላ ተከውኖ ለልጆች ማለፍ በሚችልበት መልኩ ኢትዮጵያን አክሎና መስሎ እንደተሠራ ገልጸዋል።

አሁን ባለው መንግሥት የዓድዋ ድል መታሰቢያን ማርከስ ማለት የአባቶቻችንን አጥንት እና ደም ማርከስ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ኢትዮጵያን ከነክብሯ ከነነጻነቷ ለልጆቻችን ማሸጋገር እንዲቻል እንደዚህ ያለ መታሰቢያ በእጅጉ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

## “የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ለሰላም...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የሚችል ነው ብለዋል፡፡

አውደ ርእዩ ላይ ከቀረበው ዲፕሎማሲያዊ ታሪክ የተረዳሁት ነገር ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ ከተለያዩ ሀገራት ጋር ጠንካራና መልካም ግንኙነትን መፍጠር እንደቻለች ነው የሚሉት ሄሌን ዢ፤ ቅኝ ያልተገዛች ብቸኛዋ የአፍሪካ ሀገር ከመሆኗ በተጨማሪ ለሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ነጻነት ተምሳሌት መሆን መቻሏን አንስተዋል፡፡

አዲስ አበባ ከተማ የአፍሪካ ኅብረት መቀመጫና የዲፕሎማሲ ማዕከል ከመሆኗ በተጨማሪ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት ማዕከል መሆኗ ኢትዮጵያ ከተለያዩ ሀገራት ጋር በሳይንስ፣ በኢኮኖሚ፣ በኮንስትራክሽን፣ በቴክኖሎጅና በሌሎችም መስኮች እያደረገች ያለውን ግንኙነት የሚያግዝ ነው ሲሉ ሄሌን ዢ ተናግረዋል፡፡

እንደ ሄሌን ዢ ገለፃ፤ በአሁኑ ወቅት ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ እድገትና ሰላም ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ያስፈልጋታል፤ ዜጎቿም ሀገራቸው ለመሥራትና ለመለወጥ ምቹ መሆኑዋን በመገንዘብ ጠንክረው ሊሰሩ ይገባል፡፡

አውደ ርእዩ የኢትዮጵያን ዲፕሎማሲ አካሄድና ብሔራዊ ጥቅሟን ለማስከበር የሄደችበትን ርቀት የሚያስረዳ ነው ያሉት ደግሞ የሄሌን ዢ ባለቤት ዌን ቲያን ናቸው።

በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ከተለያዩ ሀገራት ጋር እያደረገች ያለችው ግንኙነት የሚበረታታ ነው ያሉት ዌን ቲያን፤ የመንገድ፣ የሆስፒታል እና ሌሎች መሠረት ልማቶችን በማስፋፋት ረገድ ኢትዮጵያ ከቻይና ጋር ያላትን የሁለትዮሽ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ማጠናከር እጅጉን አስፈላጊ መሆኑን አንስተዋል፡፡

በኢትዮጵያ ለ16 ዓመታት መኖራቸውን የሚናገሩት ዌን ቲያን፤ በነበራቸው ቆይታም ከተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በጋራ እየሠሩ እንደሚገኙ ጠቁመው፤ በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ረገድ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል ብለዋል።

ኢትዮጵያ እጅጉን የምትወደድና በአስደናቂ የኢኮኖሚ እድገት ውስጥ የምትገኝ ሀገር ናት ያሉት ዌን ቲያን፤ መንግሥት የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት ተግባራዊ የሚያደርጋቸው እቅዶች መልካም መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

## የሚሠራና የሚተጋ እጅ ሀገር እንደሚቀይር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የሶማሌ ክልል በምሥራቁ ቀጣና ለሀገሪቱና ለጎረቤት ሀገራት ትልቅ የገበያ ማዕከል ሆኖ ማገልገል እንደሚችል የሚያሳይ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በአጠቃላይ በሶማሌ ክልል በተገኘው ሰላምና አመራሩ ባደረገው ጥረት ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚ መነቃቃት መታየቱን ገልጸዋል።

በክልሉ የመሠረተ ልማት ግንባታ፣ በግብርና፣ በጤና፣ በትምህርት፣ በገቢና በበጀት ዕድገት እየታየ መሆኑን አንስተው፤ ይህ ሥራ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አቅጣጫ አስቀምጠዋል።

በሶማሌ ክልል የተጀመሩት የልማት ሥራዎች ከለፋን፣ ከሠራን፣ ከጣርንና ሰላማችንን ማረጋገጥ ከቻልን ባጠረ ጊዜ ውስጥ የሰውን የሕይወት ደረጃ ከፍ ማድረግ እንደሚቻል ያሳያሉ ሲሉ ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳመለከቱት፤ ከሦስት ዓመታት በፊት ጅግጅጋ ምናልባትም ሰባትና ስምንት ኪሎ ሜትር የሚሸፍን አንድ የአስፋልት መንገድ ያላት ከተማ ነበረች። አሁን ላይ ከ40 ኪሎ ሜትር በላይ የሚሸፍን የመኪና፣ የብስክሌትና የእግረኛ መንገድ ግንባታ በመጠናቀቅ ላይ ነው። ከመንገድ አንፃር በሶማሌ ክልል ከ2 ሺህ ኪሎ ሜትር ያላነሰ መንገድ እየተገነባ ነው።

ባለፉት ሦስትና አራት ዓመታት ውስጥ በሶማሌ ክልል 68 ከተሞችና በርካታ ወረዳዎች የ24 ሰዓት መብራት እያገኙ መሆኑን አስታውቀዋል።

በጤናው ዘርፍም ከለውጡ በፊት በክልሉ ዘጠኝ ሆስፒታሎች ብቻ ነበሩ፤ ከለውጡ በኋላ ግን 11 ተገንብተዋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በጅግጅጋ የተመለከትነው ግዙፍና ሁሉም ነገር የተሟላለት ሆስፒታል ለጎረቤት ሀገራትም አገልግሎት የሚሰጥ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

የግሉ ዘርፍ ከተማ ውስጥ እየገነባ ያለው ህንፃ፣ የቤቶች ግንባታና አጠቃላይ የከተማው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሥራ ዕድል እንዳለ ያመላክታል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ይህም ክልሉ የተሟላ መንግሥት ሆኖ ሰዎችን ማገልገል የሚያስችለውን ብቃት እየፈጠረ መሆኑን ያሳያል ብለዋል።

በጅግጅጋ ከተማ በቀጣይ ብዙ ዛፍ መትከል፣ አካባቢውን ማጽዳትና ከዲዛይን ውጪ ያሉ ቤቶችን ማስተካከል እንደሚገባ ጠቁመው፤ ይህ ከሆነ ጅግጅጋ በሚቀጥሉት አምስትና 10 ዓመታት አማራጭ ዋና ከተማ መሆን እንደምትችል ገልጸዋል።

በጉብኝታቸው የእድሳት ሥራ የተከናወነለትን የጅግጅጋ ሼህ ሀሰን ያባሬ ሪፈራል ሆስፒታልን፣ ሸበሌ ዞን ቤርዓኖ ወረዳ እየለማ ያለውን የመስኖ ልማት ሥራ፣ አዲሱን የክልሉን ምክር ቤት ሕንፃና ሁለተኛው ዙር የጂግጂጋ ከተማ የንፁህ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት የሥራ እንቅስቃሴን ተመልክተዋል።

በሶማሌ ክልል ጎዴ ከተማ አዲስ የተገነባውን ኡጋስ ሚራድ አውሮፕላን ማረፊያን መርቀው የከፈቱ ሲሆን የተለያዩ የልማት ሥራዎችንም ጎብኝተዋል።

በተጨማሪም ከቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው ጋር የጅግጅጋ ዱቄት እና ዳቦ ፋብሪካን አስመርቀዋል፤ ፋብሪካው በቀዳማዊት እመቤት ጽሕፈት ቤት እየተሠሩ ካሉ ደሃ ተኮር ሥራዎች አንዱና በመላው ሀገሪቷ እየተሠሩ ከሚገኙ 12 መሰል ፋብሪካዎች ስምንተኛው መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስታውቀዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለትምህርት መሰረተ ልማቱ እድሳትና ግንባታ ውጤታማነት!

መንግስት የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ በጥናት ላይ ተመስርቶ ለማከናወን ከያዛቸው ተግባራት መካከል የትምህርት መሰረተ ልማቶች እድሳትና ግንባታ ይጠቀሳል፡፡ ለትምህርት ቤቶቹ የሚያስፈልጉ እንደ ውሃ፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ፣ ወዘተ ያሉት የትምህርት መሰረተ ልማቶች አለመኖር በተማሪዎች ትምህርት አቀባበል ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚያሳርፍ ይታመናል፡፡

የትምህርት ሚኒስቴር ትምህርት ቤቶች ሊኖራቸው የሚገባ መሰረተ ልማቶችን መፈተሻ ቅጽ አዘጋጅቶ ባደረገው ጥናትም ይህንኑ አረጋግጧል፡፡ በጥናቱ ከመንግስት አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወደ 49 ሺ የሚሆኑት ተካተዋል፡፡ በጥናቱ መሰረትም ስድስት ትምህርት ቤቶች ብቻ ናቸው የተሟላ መሰረተ ልማት ያላቸው ሆነው የተገኙትና ከደረጃ አራት ትምህርት ቤቶች ተርታ መሰለፍ የቻሉት፡፡

አራተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውሃ፣ ጥሩ የመጫወቻ ስፍራ ፣ ንጽህናቸው የተጠበቀ ፣ የተማሪ ክፍል ጥምርታቸውም 40 ተማሪ በክፍል የሆነ ናቸው፡፡ ሦስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙት ደግሞ መጥፎ የሚባሉ አይደለም፤ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ላይ ያሉት ትምህርት ቤት ሊባሉ የማይችሉ ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት ከትምህርት ቤቶቹ በአጠቃላይ ደረጃን የሚያሟሉት የሀገሪቱ ትምህርት ቤቶች ዜሮ ነጥብ ዜሮ ሁለት በመቶ አካባቢዎቹ ብቻ ናቸው፡፡ ይህ እጅግ ትልቅ ጉድለት ነው፡፡

በመንግስት በኩልም ይህን አስከፊ ሁኔታ መቀየር እንደሚያስፈልግ በጽኑ ታምኖበት ባለፈው ሰኔ ወር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በተገኙበት በትምህርት መሰረተ ልማት ላይ ለውጥ የማምጣቱ ዘመቻ በይፋ ተጀምሯል፡፡ ይህ ሥራ በመንግስት አቅም ብቻ ሊከወን እንደሚይችል ታምኖበትም ለመላው ሕዝብም የትምህርት ቤቶችን ደረጃ በማሻሻል ሥራ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግ ጥሪ ተደርጎለታል፡፡

ባለፉት ወራት በተደረገው ርብርብም ውጤት መመዝገቡን የትምህርት ሚኒስቴር ሰሞኑን አስታውቋል፡፡ እስከ አሁን 11 ሺ611 ትምህርት ቤቶች ታድሰዋል፡፡ በአዳዲስ ትምህርት ቤቶች ግንባታም ሦስት ሺ 180 ቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ አንድ ሺ 390 አንደኛ ደረጃ እንዲሁም 295 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአጠቃላይ ወደ አራት ሺ 871 ትምህርት ቤቶች በሕዝብ መዋጮ ተገንብተዋል፡፡

የፌዴራል መንግስት አዳዲስ 50 ሞዴል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ለመገንባት ያቀደ ሲሆን፣ ከእነዚህም መካከል ከርዳታ ድርጅቶች ጋር በመሆን የ16ቱ ግንባታ ተጀምሯል፡፡ በዚህ ዓመት ደግሞ የአራቱ ግንባታ ይጀመራል፡፡

እስከ አሁን የተከናወነው ተግባር በአምስት ዓመት በትምህርት ቤቶች መሰረተ ልማት ግንባታ በኩል ለመድረስ የታሰበውን ዕቅድ ማሳካት እንደሚቻል ያመላከተ መሆኑ በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ተጠቁሟል፡፡ እነዚህ የትምህርት ቤቶችን ደረጃ የማሳደግ ስራ ውጤቶች ባለፉት ሁለት ዓመታት በሚኒስቴሩ ከተከናወኑ የተሳኩ ተግባራት መካከል መጠቀስ ችለዋል፡፡ መንግስት መውሰድ የጀመረው ርምጃ ከጅምሩ ለውጥ ማምጣት የሚያስችለው ውጤት ማሳየቱ ርብርቡን ከነግለቱ አንዲቀጥል በማድረግ የታሰበው ላይ መድረስ አንደሚቻል ያመላክታል፡፡

እንደሚታወቀው፤ ሀገሪቱ ለሁሉም መሰረተ ልማት ሊሆን የሚችል ሀብት የላትም፤ ያላትን ሀብት ቅድሚያ ለሚሰጠው ጉዳይ ነው የምታውለው፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ቀደም ሲል የተጀመሩትን ለማጠናቀቅ እንጂ ለአዳዲስ ፕሮጀክቶች ሊውል የሚችል ብዙም ሀብት የላትም፡፡ ለፕሮጀክቶች ግንባታ የውጭ ብድርና ርዳታ ማማተሩም አዋጭ አይደለም፡፡

ስለሆነም ኢትዮጵያ ያላት ትልቅ አቅም ሕዝቧ ነው፤ ሕዝቧን ይዛ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን ገንብታለች፤ እየገነባችም ትገኛለች። መንግስት ለትምህርት መሰረተ ልማት ግንባታና ማደሱ ሥራም መላውን ሕዝብና ባለሀብቶች.ወዘተ እያስተባበረ ያለውም ለዚሁ ነው፡፡ በትምህርት ዘርፍ ጥራትን ለማምጣት ወሳኝ ከሆኑት ጉዳዮች መካከል አንዱ የሆነውን የዘርፉን መሰረተ ልማት ለማሟላትም ይህን መንገድ መጠቀሙ ትክክለኛ አቅጣጫ ነው፤ ኅብረተሰቡ የትምህርት ሥራውን በባለቤትነት እንዲከታተለው ለማድረግም ያስችላል፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር ለጋሾችን በማስተባበር ጭምር ሞዴል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ለመገንባት የጀመረው ጥረት እንዲሁም መላውን ሕዝብ፣ ባለሀብቶችንና ሌሎች የልማት አጋሮችን በማስተባበር መሰረተ ልማቶቹን ለማሟላት እንዲሁም መሰረተ ልማቶቹ የተሟላላቸውን ትምህርት ቤቶች ለመገንባት የጀመረው ርብርብ ስኬት እያስመዘገበ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡ ሕዝቡን በተለይም በውጭ ሀገሮች ጭምር ያለውን ኢትዮጵያዊ በልማቱ ለማሳተፍ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ብዙ ተሰርቷል፤ ይህም ለተገኘው ለውጥ የራሱን ሚና ተጫውቷል ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

ይህን ውጤታማ ተግባር የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ አሁንም ከተለመደው መንገድ ወጣ ያሉ አቀራረቦችን መከተልን ያስፈልጋል፡፡ በተለይ ዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን፣ ማኅበራዊ ሚዲያዎችን፣ ታዋቂ ሰዎችንና አንቂዎችን፣ ወዘተ ለመጠቀም የበለጠ ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡

በዚህ ዘመን እነዚህ መንገዶች ርዳታ በፍጥነት ለማሰባሰብ ያላቸው አቅም ከፍተኛ ስለመሆኑ ባለፉት ዓመታት በዚህ መንገድ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች ድጋፍ የተገኘበት ሁኔታ ያመላክታል፡፡ በተለይ በውጭ ሀገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የተማሩባቸውን ትምህርት ቤቶች እንዲያድሱ፣ ባደጉባቸው አካባቢዎች አዳዲስ ትምህርት ቤቶች እንዲገነቡ ለማድረግ ወሳኝ እንደመሆኑ ለዚህ ስራ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ያስፈልጋል፡፡

ከእስካሁኑም በላይ ሁሉም የማኅበረሰብ ክፍል ለዚህ ታላቅ ሀገራዊ ጥሪ ተግባራዊ ምላሽ እንዲሰጥ መሥራት ይኖርበታል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በዓለምም በአፍሪካም ታላቅ የተሰኘውን የዓባይ ግድብ የገነባ ነው፡፡ ይህን ማድረግ የቻለ ሕዝብ የትምህርት ጥራት አንዱ ችግር ተደርጎ የተለየውን የትምህርት ቤት መሰረተ ልማት ችግር መፍታት አይሳነውም!

ዋናው ነገር ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል በልማቱ ማሳተፍ ነው፣ ዘመኑ ደግሞ ይህን ለማድረግ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች ባለጸጋ የሆነበት እንደመሆኑ ይህን በመጠቀም ርብርቡ እንዲጠናከር ማድረግ ይገባል፡፡

**አዲስ ዘመን**
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የእናት አፍሪካ ተስፋና ተግዳሮቶች

ግርማ መንግሥቴ

የአፍሪካ ሕብረት ለ37ኛ የመሪዎች ጉባኤው እየተንደረደረ ነው። ባለፉት 36 ጉባኤዎቹ ሲያደርግ እንደ ነበረው ሁሉ በዚህኛውም በተለያዩ አጀንዳዎች ላይ ተነጋግሮ ውሳኔዎችን ያሳልፋል ተብሎ ይጠበቃል። የተወሰኑትን ውሳኔዎች ወደ መሬት ማውረዱ ላይ አባል አገራቱም ተመሳሳይ ርምጃ ስለ መውሰዳቸውም እንደዛው።

ለዛሬ ግን ስለ አንዳንድ አፍሪካዊ ማንነቶች የአፍሪካን ማንነቶች ትንሽ እንድንጨዋወት ወደድኩ። እንደሚታወቀው አፍሪካ የጥቁር አፈርና የጥቁር ሕዝብ ምድር ነች። በመሆኗም በብዙዎች "እናት አፍሪካ" (ማዘር አፍሪካ) በመባል ስትጠራ ይሰማል። ድምፃውያኑም "አፍሪካ ማማ"፤ "ማማ አፍሪካ" ወዘተ እያሉ ሲያዜሙ መስማት የተለመደ ነው። እዚህ ጋ አህጉሪቱ ለዚህ ማኅበራዊ ማዕረግ ያበቃት ምንድን ነው? ብሎ መጠየቅም ተገቢ ነው።

በመሰረቱ አፍሪካ "ልዩ ምድር ነች" ሲባል ከራስነት ጋር በተያያዘ ለማንቆለጳጰስ በማሰብ አይደለም። አፍሪካን ልዩ አድርጎ የመግለፁም ሆነ በ"እናት አፍሪካ ነት" ማዕረግ የመጥራት ምንጩ አህጉሪቱ በተሰጣት ፀጋ እና በታቀፈችው ተዝቆ የማያልቅ ሀብት ብቻ አይደለም፤ በርግጥ ተዘርፎ እንኳን የማያልቅ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ (ወይም/እና፣ መንፈሳዊ እና ቁሳዊ) ሀብት ባለቤት ናት። በመሰረቱ አፍሪካ ጥቅጥቅ ያለ ሀብት ባለቤት ነች። ይህ የሀብት ጥቅጥቅታ ደግሞ በሁሉም እንጂ በተፈጥሮውና በሰው ሰራሹ ብቻ አይደለም። በመሆኑም፣ "ማማ አፍሪካ" ልዩ ነች ስንል በባዶ አይደለም።

የኮምቦኒ ሚስዮናውያን ካህን እና የአፍሪካ ሊቅ የሆኑት አባ ጁሊዮ አልባኔዝ የአፍሪካ ቀን (ግንቦት 17)ን በማስመልከት ከቫቲካን ራዲዮ ጋር አድርገውት በነበረ ቃለ-ምልልስ (ቫቲካንኒውስ እንዳሰራጨው)፣ ስለ አፍሪካ በረከቶች፣ ስለ ሰው ልጅ ትስስር እና የሰው ልጅ የጋራ እጣ ፈንታ እንደ ተናገሩት "አፍሪካ በእውነት ለሰው ልጅ በረከት እንደሆነች በፅኑ አምናለሁ፥ አፍሪካ በርካታ አቅም ያላት አህጉር እና የአያት ቅድመ አያቶች ጥበብ መገኛ አህጉርም ጭምር፤ በጭራሽ ድሃ አይደለችም፥ ደሃ አህጉር አይደለችም፥ ነገር ግን በብዙ ሴራ ሰዎች ያደኸዩዋት አህጉር ነች።"ብለዋል

"የውጭ ኃይሎች 'የጨዋታውን ሕግ መቀየር በሚፈልጉ' በሲቪል ማኅበራት፣ በንቅናቄ አራማጆች፣ በተራው ሕዝብና እና በተለያዩ ኃይላት ላይ ለአሁኑም ሆነ ለወደፊቱ ሲሉ ኢንቨስት ማድረግ አለባቸው" ፤"በሌላ አነጋገር አፍሪካን በአዎንታዊ መልኩ ማየት አለብን" ሲሉ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

**"አፍሪካ በእውነት ለሰው ልጅ በረከት እንደሆነች በፅኑ አምናለሁ÷ አፍሪካ በርካታ አቅም ያላት አህጉር እና የአያት ቅድመ አያቶች ጥበብ መገኛ አህጉርም ጭምር፤ በጭራሽ ድሃ አይደለችም**

እናት አፍሪካ (ማማ አፍሪካ) ለእሷ፣ ለራሷ ይሆኗት ዘንድ አልታደሉም እንጂ የሳይንቲስቶች ምድር ነች። የነጩን ምድር እያበለፀጉ ያሉትን ጥቁር ሳይንቲስቶች "ቤቱ ይቁጠራቸው" ከማለት ያለፈ ምንም ማለት አይቻልም። ከዚህ አኳያ ናይጄሪያ እየከፈሉ ያሉትን ዋጋ ብቻ ማስታወሱ ይበቃል።

እርግጥ ነው፣ ከአጠቃላይ መሬት 20 በመቶውን የምትሸፍነው፣ 30·3 ሚሊዮን ኪሎ ሜትር ስኩር ስፋት ያላት፣ ከ1·4 ቢሊዮን (የ2021 ጥናት እንደሚያሳየው) በላይ ሕዝብ የያዘችው (ከዓለም 2ኛዋ)፣ ከዓለም ሕዝብ 18 በመቶው በእጇ ያለ፣ ከእሲያ ቀጥሎ 2ኛዋ ሰፊ አህጉር፣ ከ1250–3000 የሚደርሱ የራሷ ቋንቋዎች (native languages) ያሷት፣ በ2022 ጂዲፒዋ 2.96 ትሪሊዮን ዶላር የነበራት ዛሬም አፍሪካ ደሀ ነች።

ነገር ግን፣ በአንድ የአፍሪካ ሕብረት የመሪዎች ጉባኤ ላይ የኡጋንዳው ፕሬዚዳንት ሙሴቬኒ እንደ ተናገሩት፤ ከአፍሪካ የሚጋዘው የአትክልት ምርት እንግሊዞችን ሲያንበሸብሽ መንግስታቱን አቶጁሯል። አሜሪካ ከአፍሪካ በሚሄዱ ኦርጋኒክ ምርቶች ሁሌም ጥግብ እንዳለች ነው። ወዘተርፈ . . . የዚህ ሁሉ ችግር መነሻው የአፍሪካ ምርቶች ፕሮሰስ ሳይደረጉ እንዳለ መሄዳቸው ነው፣ ፕሮሰስ ተደርገው (አልቆላቸው) ላለ መሄዳቸው ደግሞ ሆን ተብሎ የተሰራ ሴራ በመኖሩ ነው፤ በቃ ይሄው ነው።

አፍሪካ እንድትሆን የምትፈለገው ምርቷን እንደ ያዘች እንድትቆይና የሚፈልገው አካል በፈለገ ጊዜ እንዲዝቀው እንጂ ሌላ አይደለም። አንድ ነጭ የስነሰብ ምሁር (ፕሮፌሰር ናቸው) በአንድ አውሮፓ ውስጥ በተካሄደ ስብሰባ ላይ ሲናገሩ እንደ ተሰማው፤ የነጩ ዓለም ያለ አፍሪካ ምንም ዋጋ የለውም። ለነጩ ዓለም መበልፀግ መነሻው የአፍሪካ ሀብት ነው። በመሆኑም፣ የነጩ ምድር (አውሮፓና በውስጠ ታዋቂ አሜሪካንን ጨምሮ) ብልፅግና እንዲቀጥልና የበለጠም እየበለፀገ እንዲሄድ ከተፈለገ አፍሪካ ወሳኝነት አላት። በአፍሪካ ውስጥ ያሉት ተቋሞቻችን የተቋቋሙበት ዋና ዓላማ ይሄንን ለማስጠበቅ በመሆኑ በዚሁ መስመር ሊንቀሳቀሱ ይገባል። የአፍሪካ እምቅ ሀብት ስለ አውሮፓ ብልፅግና ሲባል በእምቅነቱ ተጠብቆ ሊቆይ ይገባል።

አሁን አሁን ከየጓዳው እየወጣ በአደባባይ የሚነገረው እውነታ ይኸው ነው፣ የሙሴቬኒ የአፍሪካ ሕብረት አዳራሽ ቁጭትም ከዚሁ ጋር የተያያዘ አይደለም ለማለት የመከራከሪያ አቅም የለም። እናት አፍሪካ ዛሬ ያለችበትን ሁኔታና ይዞታ በቅርብ ለተከታተለ እውነትም ከላይ ያልነውን የማስጠበቅ ሁኔታ ያለ ይመስላል። አህጉሪቷ ከዳር እስከዳር እየተናጠች ነው። የቱ ጋ ሰላም እንዳለ እና እንደ ሌለ እንኳን ለመለየት በማያስችል ደረጃ ትርምስ አለ።

ግድያ፣ ሞት፣ ረሀብ፣ ጉስቁልና፣ በሽታ፣ የመልማት ጥያቄዎች፣ የከፋ የምግብና ንፁህ የመጠጥ ውሀ እጥረት፣ ስራ አጥነት . . . የአህጉሪቱ ቁልፍ ችግሮች ናቸው፤ የዘንድሮው

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# ተጠየቅ

# ‹‹ዘመናዊ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ የአሰራር ስርዓት ባለመዘርጋቱ የመታወቂያ አሰጣጥ ችግር ፈጥሯል››

አቶ ዮናስ ዓለማየሁ-
የአዲስ አበባ ከተማ የሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር

ሞገስ ተስፋና ሙሉቀን ታደገ

የወሳኝ ኩነት መረጃ የሕዝብን ማኅበራዊና ተፈጥሯዊ ኩነት ሰንዶ ለማስቀመጥ አስፈላጊ ነው፡፡ ለአንድ ሀገር ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገትም የሚኖረው ስትራቴጂክ አስተዋጽኦም ከፍያለ ነው።

በሀገራችን የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ከተጀመረ ከ80 ዓመታት በላይ አስቆጥሯል። በዚህ ረጅም እድሜው ግን በሚጠበቀው መልኩ መዘመን የቻለ አይደለም። የዕድሜውን ያህል የሚመዘን አሁናዊ ቁመናም የለውም።

በዛሬው እትማችን የዚሁ ሀገራዊ ተቋም አካል የሆነውን፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ አድርጌዋለሁ በሚለው ሪፎርም ምንነት ዙሪያ፣ ሪፎርሙ ይዟቸው ስለሚመጣቸው አዳዲስ አሰራሮች እና ሊፈታቸው ስለሚችላቸው የአግልግሎት አሰጣጥ ችግሮች ወዘተ ጥያቄዎችን አንስተን ከኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቶ ዮናስ ዓለማየሁ ጋር ቆይታ አድርጓል፡፡ መልካም ንባብ፡፡ !!

**አዲስ ዘመን፡- ኤጀንሲው ባለፉት ወራት ምን አቅዶ ምን ሰራ?**

**አቶ ዮናስ፡-** ተቋሙ ባለፈው ዓመት ጀምሮ መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት አለበት ተብሎ በከተማ አስተዳደሩ ትኩረት ከተሰጣቸው ተቋማት ግንባር ቀደሙ ነው፡፡ ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ ከዋና መስሪያ ቤት እስከ ወረዳ ድረስ ያሉ በርካታ ጉዳዮችን ለመቀየር በቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ በሰው ኃይል አደረጃጀት፣ ምቹ የስራ ከባቢ በመፍጠር ብዙ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

እንደ ተቋም፣ ተቋም ሁለት ዋና ዋና ስራዎች አሉት፣ አንደኛው የወሳኝ ኩነት ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ስራን መምራት ነው፡፡ በስድስት ወር ውስጥ የተሰራው ስራ በተለይም በወሳኝ ኩነት ምዝገባ እንደ ከተማ አስተዳደር ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገር ከፍተኛ ውጤት የተመዘገበበት ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ትልቁ ምክንያት ከአዲስ አበባ ጤና ቢሮ፣ ከአዲስ አበባ መድሃኒትና እንክብካቤ ባለስልጣን እና ከከተማ አስተዳደሩ በጋር መስራቱ፣ በግልም በመንግስት ጤና ተቋማት ላይ ሞትና ልደትን መመዝገብ የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት መመዝገብ መቻሉ ነው፡፡

አሁን ላይ ከ70 በላይ በሚሆኑ የጤና ተቋማት የልደትና የሞት ምዝገባ በማከናወን የምስክር ወረቀት ይሰጣል። ይህ መሆኑ በከተማዋ ያለውን የልደትና የሞት ምዝገባ ላይ ውጤት አምጥቷል፡፡ ሌሎች ሁነቶችም በተመሳሳይ የጋብቻና ፍች ምዝገባ ቢታይ ከዓለፉት ተመሳሳይ ዓመታት ጋር ሲታይ ከ50 በመቶ በላይ ብልጫ አለው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በሪፎርሙ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል? ለዘመናዊ ሀገር ግንባታ አስተዋጽኦው እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ዮናስ፡-** የወሳኝ ኩነት ምዝገባ መቶ ፐርሰንት ደርሶ መንግስት እነዚህን መረጃዎች ባልያዘበት ሁኔታ ዘመናዊ ከተማና ዘመናዊ ሀገር መገንባት አይቻልም፡፡ በአንድ ሀገር ውስጥ ምን ያህል ሰው ተወለደ፣ ሞተ፣ ተጋባ፣ ተፋታ፣ የሚለው መረጃ እስከሌለ ድረስ የሀገሪቱንና የመዲናይቱን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ለመምራት ያስቸግራል፡፡ ይህን መረጃ በሚፈለገው መንገድ ለማከናወን በትምህርት ቤት ጭምር ሕጻናት ስለ ወሳኝ ኩነት እንዲገነዘቡ በማድረግ የልደት ካርድ በትምህርት ምገባ እንደ አንድ ማስረጃ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ባለፉት ስድስት ወራት የዲጂታል ምዝገባ አፈጻጸሙ ከመቶ ፐርሰንት ተሻግሯል፡፡ በወረዳና በማዕከል ከተሰጡት አገልግሎቶች ውስጥ በስድስት ወሩ 93 በመቶ የሚሆነው ዲጂታል ነው፡፡ የማንዋል መታወቂያ የተሰጠው 15 ሺ ገደማ ነው፡፡ ይህም የሆነው ወደ ዲጂታል አሰራር ባልገቡ በሶስት ክፍለ ከተሞች የሚገኙ 15 የሚሆኑ ወረዳዎች ላይ ነው፡፡ ለዚህ ምክንያቱም የመሰረተ ልማት ችግር ነው፡፡

በተለይም ከሁለት ዓመት በፊት በማንዋል የተሰጠው መታወቂያ 89 በመቶ ገደማ ነበር፡፡ ይህ አሁን ላይ ተቀልብሷል፡፡ በሪፎርሙ በ104 ወረዳዎች ላይ ዲጂታል አገልግሎት እየሰጠ ነው፡፡ በእነዚህ ወረዳዎች በምንም መልኩ ማንዋል አገልግሎት የለም፡፡

በሪፎርሙ አንዱ ትኩረት የተሰጠው የሚሰራጩ ህትመቶች መታወቂዎችና አገልግሎቶች ኦዲት መደረግ አለባቸው የሚል ነው፡፡ በ2014 ሪፎርሙ ሲጀመር መታወቂያ ጭምር ኦዲት ተደርጎ ነበር፡፡ የ2015 የግማሽ ዓመት በራሱ አቅም ኦዲት ማድረግ ተችሏል፡፡ በተደረገው ኦዲት ስራ 63 አመራር፣ ቡድን መሪዎችና ባለሙዎች ተጠያቂ ሆነዋል፡፡ የተጠያቂነት ደረጃውም ከዲስፐሊን እስከ ወንጀል ድረስ ነው፡፡

12 ሰዎች በወንጀል፣ 83 የሚሆኑ የተቋሙ ሰራተኞች፣ ደላሎችና ተገልጋዮች በስነ ምግባርና ጸረ ሙስና በተደረገው ክትትል በሕግ እንዲጠየቁ ተደርጓል፡፡ ከነዚህ ውስጥ 34ቱ ሀሰተኛ ሰነድ ይዘው የቀረቡ ባለጉዳዮች ናቸው። ሁለቱ ወረዳ ላይ የተያዙ ሲሆን 32 በማዕከሉ ሰነድ ሲረጋገጥ ሀሰተኛ ማስረጃ ይዘው የቀረቡ ናቸው። ካርዶች እየተሰራጩ ያሉት በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት በኩል ሚስጥራዊነታቸው በተጠበቀ መልኩ ነው፡፡ በተተገበረው ቴክኖሎጂ ሀሰተኛ ሰነድን መለየት አስችሏል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ተቋሙ በሪፎርም ስራው ውስጥ የስያሜ ለውጥ ማድረጉ ምን ውጤት አስገኘ? እንደ ከተማ አስተዳደርና እንደ አገር ምን ጥቅም አለው? የነበሩ ችግሮችስ ምን ነበሩ?**

**አቶ ዮናስ፡-** የስያሜ ለውጥ የተደረገው ዓለም አቀፋዊ ነባራዊ ሁኔታውን ያማከለ እንዲሆን ለማድረግ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ እና በተባበሩት መንግስታት ቻርተር እንደተመላከተው ዜጎች የወሳኝ ኩነት አገልግሎት የማግኘት ሰብአዊ መብት አላቸው፡፡ ዓለም አቀፉ ተሞክሮ ሲታይ ወሳኝ ኩነት ተብሎ የተሰየመበት የስያሜ አሰጣጥ ከዓለም አቀፍ ልምዱ ጋር በተወሰነ መልኩ ተዛብቷል፡፡ ወሳኝ ኩነት የሚሉት የሚመዘገቡት ኩነቶች ናቸው፡፡

ሁለት አይነት ወሳኝ ኩነቶች አሉ፤ አንደኛው በተፈጥሮ የሚከሰት እንደ ሞትና ልደት ያሉት ናቸው፡፡ ሌላው ማኅበራዊ የሚባሉ እንደ ጋብቻ ፍቺና ጉዲፈቻ የመሳሰሉት ኢትዮጵያ ተቀብላ የምትተገብራቸው ሰባት የሚሆኑ የወሳኝ ኩነቶች መጠሪያዎች ናቸው፡፡ ስርዓቱ ግን የሲቪል ምዝገባ ስርዓት ወይም ሲቪል ሪጅስትሬሽን ሲስተም ነው፡፡

ስራው የሚመራው በኤጀንሲ ወይም ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ ሳይሆን ዓለም ላይ ባለው መጠሪያ የሲቪል ምዝገባ ተቋም በሚባል ነው፡፡ እንደ ሀገርም ስምምነት ላይ የተደረሰው በዚህ ስያሜ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ክልሎች ጭምር ስያሜውን እየቀየሩ ነው፡፡ ስያሜው እንዲቀየር የተደረገው ዓለም አቀፉ እውነታን መሰረት በማድረግ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከወሳኝ ኩነት ጋር በተያያዘ በሕብረተሰቡ ውስጥ ያለው ዕይታ ምን ይመስላል ?**

**አቶ ዮናስ፡-** ወሳኝ ኩነት ሲባል ማኅበረሰቡ ወረዳ ላይ በመሄድ የሚስተናገድበት፤ ጥሩ አገልግሎት የሚያገኝበት ሳይሆን ቀበሌ ከሚለው አስተሳሰብ የሚያያዝ ነው። አዲስ አበባ ውስጥ ቀበሌ የሚባል አደረጃጀት የለም። ነገር ግን ወረዳ የሚለው ስም ማኅበረሰቡ ለአገልግሎት ሂዶ የሚንገላታበት አድርጎ ተስሏል፡፡ ይህን አስተሳሰብ ለመቀየር የግድ ከስም ጀምሮ ‹ሪብራንድ› መደረግ አለበት ተብሎ ለአዲስ አበባ ምክር ቤት ጥያቄ ቀርቦ ሲቪል ምዝገባና ነዋሪነት አገልግሎት እንዲሆን ተደርጓል፡፡

ተቋሙ የማንነት አስተዳደር ላይ የሚሰራ ነው፡፡ ይህም ማለት ግለሰቦችን ማንነታቸውን መዝግቦ እውቅና የሚሰጥ ነው፡፡ "አበበ" የሚባል ሰው "አበበ" መሆኑን አረጋግጦ ሰነድ የሚሰጠው ይህ ተቋም ነው፡፡ "አበበ" ይህን ማስረጃ ከወሰደ በኋላ ትክክለኛ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መስተጋብሩን ይጀምራል፡፡ አንድ ሰው ማን ነህ? ሲባል ስለማንነቱ የሚገልጽ ሰነድ የሚሰጠው በዚህ ተቋም ነው፡፡

ሰዎች አሰራርንና መመሪያን ያልተከተለ ሕገ ወጥ ሀብትን ለማካበት ሲሉ ማንነታቸውን ይቀይራሉ፡፡ ከሰላምና ጸጥታ አኳያ የአካባቢን፤ የሀገርን ሰላም ማወክ የሚፈልግ ሰው የመጀመሪያ ዓላማው በዚህ ተቋም የሚሰጠውን መረጃ ማስወገድ ነው፡፡ ይህም በአዲስ አበባ ነባራዊ ሁኔታ ተፈጥሮ ተስተውሏል፡፡


ፎቶ ገባቦ ገብሬ

**አሁን ላይ ከ70 በላይ በሚሆኑ የጤና ተቋማት የልደትና የሞት ምዝገባ በማከናወን የምስክር ወረቀት ይሰጣል**

ከሰራተኞች የስነ ምግባር ችግር፤ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ውስንነት፤ ጣልቃ ገብነት መኖር፤ ሕገ ወጥ ደላሎች በቀላሉ አሰራሩን የሚጠልፉበት ሁኔታ መኖርና መሰል ችግሮች ተደምሮ የተቋሙን አሰራር ተፈታትነውታል። በአገሪቱ ተጨባጭ ሰላምና ደህንነት አንጻር አዲስ አበባ ውስጥ ሊፈጠር ለታሰበው የሰላም ችግር እንደ መግቢያ በር የታሰበውም በተቋሙ ያለውን መረጃ በመጠቀም ነበር፡፡ ይህም በጸጥታ መዋቅሩና እንደ መንግስትም የተደረሰበት ስለነበር አገልግሎት መስጠት የቆመበት ወቅት ነበር፡፡ አገልግሎቱ መቆሙ ተቋሙ ራሱን እንዲያይ አድርጎታል፡፡

ካርዶች አሰራረን ተከትለው አለመሰራጨታቸው፤ የታተመ ካርድ ከብርሃንና ሰላም ጀምሮ የሚሰራጭበት ሁኔታ የቁጥጥር ስርዓት አልነበረውም፡፡ በዚህ የስርጭት ሂደቱ ስህተት ነበረበት፡፡ የማንዋልና ዲጂታል መታወቂያም በተመሳሳይ መንገድ በራሱ የሚመዘገበው ሰው ማን ነው ? የሚለው ቁጥጥር ይፈልጋል፡፡

ከሰራተኛ ጋር ተያይዞ የሚሰራውን ከማይሰራው መለየት፤ የሚያጠፋውን ማረምና መቅጣት ያስፈልጋል። የተቋሙ አስፈላጊነት በመዲናይቱ እየሰፋ ከመምጣቱ አንጻር የተቋሙ አደረጃጀት አገልግሎት ለመስጠት በቂ ስለመሆኑ፤ ኅብረተሰቡን የሚመጥን የአገልግሎት አደረጃጀት ስለመኖሩ እርግጠኛ መሆን፤ ዲጂታል መታወቂያ ለኅብረተሰቡ በቀላሉ የማይደርሰው ለምድን ነው? የሚለውን በማየት ችግሮችን መቅረፍና አገልግሎት የማሻሻል ስራ መስራት ያስፈልጋል ነበር፡፡

በጉዳዩ ዙሪያ የአዲስ አበባን ለየት የሚያደርገው የነዋሪ አገልግሎትን አብሮ ነው የሚመራው፡፡ በጡረታ ከቤታቸው የሚኖሩ ዜጎች አገልግሎት የሚያገኙት

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ተጠየቅ

## ‹‹ዘመናዊ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ የአሰራር ስርዓት...

**ከገጽ 6 የዞረ**

በውክልና ነው። በዚህ ወቅት መብታቸውን ለአልተገባ ጥቅም ይውላል ተብሎ ስለሚታሰብ ሰዎቹ በሕይወት ስለመኖራቸው የተመዘገቡበት የመንግስት ተቋም ደብዳቤ እንዲሰጥ ይገደዳል፡፡ ለማኅበራዊ ዋስትናም ደብዳቤ ይጽፋል፡፡

የሲቪል ምዝገባ ስርዓት በዲጂታል ካልሆነ በባህሪው አገልግሎቱ ወደኋላ ይቀራል፡፡ ስለዚህ አሻራ መቀበልና ማስተናገድ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ በፊት ከዜጎች አሻራ መቀበል የሚያስችል የተደነገገ ሕግ አልነበረም፡፡ ለባንክ ቢፈልግ ማጋራት የሚያስችል መመሪያ የለም፡፡ የዚህ ስልጣንና ተግባር በዚህ በአዲሱ ስያሜ ተግባርና ኃላፊነቱ ተካቷል፡፡ አሁን ላይ በተቋሙ ያለ ሕግና መመሪያ የሚሰራ ምንም ስራ የለም፡፡

የሰው ሀብት መረጃ አያያዝ በኩል መረጃው "ስካን" ተደርጎ በዘመነ መልኩ እንዲያዝ ተደርጓል፡፡ በ104ቱም ወረዳዎች የሚከናወኑ የወሳኝ ኩነትና ሲቪል ምዝገባ አገልግሎት ቀጥታ መረጃው በማዕከል ይመዘገባል፡፡ ምን ያህል፤ ሞት፤ ፍቺ፤ ልደትና መሰል ሁነቶች ይመዘገባሉ፡፡ ይህን ማድረግ የሚያስችል ሶፍት ዌር በተቋሙ ባለሙያዎች ለምቷል፡፡ በፊት የማንዋል ስራዎች በነበሩ ጊዜ አሰራሩ አስቸጋሪ ነበር፡፡ አሁን ግን ቀጥታ ሰነዱን ሲስተም ላይ አስገብቶ ማረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ ምንም አይነት የወረቀት ንክኪ የለም፡፡ አሰራሩ እንዲዘምን የተደረገው ደሞዝ በመቀየር ሳይሆን የአስተሳሰብ ለውጥ በመኖሩ ነው፡፡

በፊት በተቋሙ የነበረው አሰራር ችግር ያለበት በመሆኑ አገልግሎት ቆሟል፡፡ ይህ የቆመው በከተማ አስተዳደሩ ሊሆን ይችላል፡፡ የቆመው የቁጥጥር ስርዓት ባለመኖሩ በነበረው ችግር ነው፡፡ ሌብነት፤ ሰነድ ማጭበርበር ነበር፤ ይህን ማስተካከል ከተቻለ የተሻለ ተቋም እንሆናለን በሚል ብዙ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ አሁን ላይ በአገልግሎቱ በሕዝቡ ረክቷል ወይ ከተባለ ገና አልረካም፡፡ አሁንም በጣም ብዙ የሚቀሩ ነገሮች አሉ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ተቋሙ በ1935 ዓ.ም የተሰመረተ እንደመሆኑ መጠን በዕድሜው ልክ ዘምኗል ማለት ያስደፍራል?**

**አቶ ዮናስ፡-** ዕድሜውን የሚመጥን ተቋም እንዲሆን ባለፉት ዘጠኝ ወራት መሰረት የመጣል ስራ ሰርተናል፡፡ መሰረት ተጥሏል? ብለህ በቀጣይ ሰኔ ወር ላይ ብጠይቀኝ በእርግጠኝነት አዎ ብዬ በልበ ሙሉነት እመልሳለሁ። መሰረት መጣል ማለት አንዱ ሕግ ማውጣት፤ የሰው ኃይል፤ የአሰራር ስርዓት ተቋማዊ ማድረግ ነው፡፡ የሕግ ማውጣት ጉዳይ አልቋል፡፡ ካሁን በኋላ የሚቀየር አሰራር የለም፡፡ የአሰራር ስርዓቱ በሙሉ ወደ ሕግ ማቀፍ ገብቶ መሰረት ይዟል፤ አንዳንዶቹም ትግበራ ላይ ገብተዋል፡፡

ሕጎቹ ወደ እንግሊዝኛና ብሬልም እየተተረጎሙ ነው። በቴክኖሎጂ ትግበራም የተያዙት ፕሮጀክቶች ሲጠናቀቁ ለሌሎች ተቋማት ጭምር የሚተርፍ ነው፡፡ ከወራት በኋላ ወደ ስራ የሚገባ ግንባታው የተጠናቀቀ የዳታ ማዕከል አለ፤ በተደጋጋሚ ሲስተም በመቆራረጥ ለአገልግሎቱ ችግር የሆነው የዳታ ማዕከሉ ማዘጋጃ ቤት ነው ያለው፡፡ ይህ ዳታ ማዕከል ከ15 ዓመት በፊት ውስን ለሆኑ ተቋማት የኢሜልና የዌብሳይት አገልግሎት ይሰጥ ነበር፡፡ ከዚህ ዳታ ተነስቶ ወደ ወረዳ የሚደረስ መስመር አልነበረም፡፡ ሁሉም ተቋማት በአንድ የዳታ ማዕከል አገልግሎት ሲሰጡ የመጨናነቅ ሁኔታ ነበር፡፡

አሁን ላይ ይህን መጨናነቅ ለማስቀረት በአንድ ማዕከል ለማከናወን መስመሩ እንዲዘረጋ ተደርጓል። "የወረዳ ኔት" የሚለውን ስያሜ በመተው "ሲአርኔት" በሚል የራሱን የቻለ ሲስተም ተዘርግቷል፡፡ ይህን መሰረተ ልማት የሚያሻሽል ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ከሁለት ወር በፊት በግማሽ ቢሊዮን ብር ፕሮጀክት ተጀምሮ ቁሳቁሶች እየገቡ ነው፡፡ ኔትወርክ ሲቋረጥ የት አካባቢ እንደሆነ የሚጠቁም ሲስተም እየተዘረጋ ነው። ከአንድ ወር በኋላ ሙሉ በሙሉ ይጠናቀቃል፡፡

ለተቋሙ አገልግሎት በተሰጠው ትኩረት መሰረት የፊትና የአይን አሻራ ከዚህ በፊት አልነበረም፡፡ አሁን ላይ በሁሉም ወረዳዎች ገብቷል፡፡ ምክንያቱም ተቋሙ ካልተሻሻለ ለውጥ ሊመጣ አይችልም፡፡ ስለዚህ ይህን ታሳቢ ያደረገ ሲስተም እየለማ ነው፡፡ ወደ አገልግሎት ሲገባ አገልግሎት በኦንላይን የሚሰጥበት ስርዓት ለመፍጠር ነው። ለዚህ ደግሞ አሻራ ሊቀበል የሚችል ኮምፒውተር መኖር አለበት፡፡

አንዳንድ ወረዳ ላይ ያሉ ኮምፒውተሮች ከእጅ ስልክ አይበልጡም፤ ካሉት ወረዳዎች ብቁ የሆነው ኮምፒውተር ብቁ የሚባለው መቶ አይሞላም፡፡ ይህን ችግር ለመፍታት



ከከተማ አስተዳደሩ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ጋር በመነጋር ዘመናዊ የሆኑ ስምንት መቶ ኮምፒውተሮችን ለመግዛት እየተሰራ ነው፡፡ እነዚህ ኮምፕዊተሮች ዋናው መስሪያ ቤት በሚቆጣጠርበትና ክትትል ሊያደርግ በሚችልበት መልኩ ተዘጋጅተው ይሰራጫሉ፡፡

የ80 ዓመት እድሜ ያለው ተቋም ግን በዚህ ደረጃ መገኘት አልነበረበትም፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያ በ1935 በሰርተፊኬት ጋብቻ ስታስፈጽም ሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች በቅኝ ግዛት ስር ነበሩ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ነዋሪው በተለይም በልደት ካርድ ስርጭት ላይ ውስንነት እንዳለ ከፍተኛ ቅሬታ ያሰማልና እርሶ ይህን እንዴት ይመለከቱታል?**

**አቶ ዮናስ፡-** የወሳኝ ኩነት ምዝገባ እዛው ተመዝግቦ ወዲያውኑ ሰርተፊኬት ይዞ የሚሄደው አዲስ አበባ ውስጥ ብቻ ነው፡፡ ሌሎች ክልሎች ብቻ ሳይሆን በሌሎች ሀገሮች የምስክር ወረቀት ይቆያል፡፡ ለምሳሌ አሜሪካ ላይ ህጻን በጤና ጣቢያ እንደተወለደ ለአገልግሎት መስሪያ ቤቱ መረጃ ይሰጥና የምስክር ወረቀቱ ቆይቶ ይደርሳል፡፡

ኤጀንሲው የሚሰጠው የወሳኝ ኩነት የምስክር ወረቀት የሚታተመው ብርሃንና ሰላም ማተሚ ድርጅት ነው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን የሚታተመው በሚስጥራዊ ህትመት ክፍል ነው፡፡ ሀገሪቱ ውስጥ የሚከናነወኑ የወሳኝ ኩነትና ሌሎች ሚስጥራዊ ካርዶች በሙሉ የሚያትመው ይህ ድርጅት ነው፡፡ ስለሆነም ተቋሙ እንደማንኛውም ተቋም የማተሚያ ማሽን ብልሽት ይገጥመዋል፡፡ በዚህ ወቅት በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ጫና ይፈጠራል፡፡

የልደት ሰርተፊኬት በትምህርት ቤቶች በንቅናቄ ለመስጠት ሞክረን ነበር፤ ነገር ግን የካርድ እጥረት አጋጠመን፡፡ ማተሚያ ቤቱም ሕትመቱን በወቅቱ ማድረስ አልቻለም፤ የዲጂታል ማንነት ምዝገባ በባህሪው ውድ ነው፡፡ የማሽን ብልሽት በሚገጥምበት ወቅት እስከ ዱባይ ድረስ በመላክ ጥገና ይደረግ ነበር፡፡ የአጭር ጊዜ መፍትሄ የተወሰደው ክፍለ ከተሞች እንደየአቅማቸው እንዲገዙ ነው፡፡ ምክንያቱም ያለ ካርድ ምንም ማድረግ አይቻልም፡፡

አሁን ላይ ከካርድ ሕትመት ጋር በተያያዘ ብዙም ችግር የለም፡፡ ምን ያህል ካርድ ተላከ? ምን ያህል ታትሞ ለተገልጋይ ተሰጠ? የሚለው ማዕከል ላይ ባለው መቆጣጠሪያ መከታተል ተችሏል፡፡ ነገር ግን ቴክኖሎጂው የሚፈጥረው ችግርም አለ፤ ፕሪንተሩ ከተበላሸ አገልግሎት ይቆማል፡፡ አንድም ሰው የወረቀት መታወቂያ መያዝ የለበትም በሚል ወደ ዲጂታል መታወቂያ እየተቀየረ ነው፡፡ በዚህም እስካሁን አንድ ነጥብ 52 ሚሊዮን ሕዝብ ዲጂታል መታወቂ የያዘ ሲሆን 2 ነጥብ 5 ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ ደግሞ ተመዝግቧል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በሪፎርም ስራው የሰራተኛው ደሞዝ አሁን ካለው የኑሮ ውድነት ጋር እንዲጣጣም የተደረገ ነገር አለ ?**

**አቶ ዮናስ፡-** እኔ የማልስማማበት አንድ ነገር አለ፡፡ ይህም አንድ ባለሙያ ጥሩ አገልጋይ ሆኖ በተመደበበት ቦታ ላይ እንዲያገለግል ደሞዝ ወሳኝ ነው የሚል እምነት የለኝም። ከእኛ ተቋም የተሻለ ደሞዝ የሚከፈላቸው ተቋማት አሉ። ነገር ግን አሁንም ሌብነትና በርካታ ችግሮች አሉባቸው። የተሻለ ገንዘብ እያገኙ በስነ ምግባር የማያገለግሉ አሉ። ስለዚህ በአግባቡ አገልግሎት ለማግኘት ከደሞዝ ጋር የሚያገናኘው አስተሳሰብ በልኩ መታየት አለበት፡፡

የተሻለ መከፈሉ ያነሳሳል ነገር ግን የሚከፈለኝ ደሞዝ ትንሽ ነውና ልስረቅ የሚለው አስተሳሰብ በተለይም ኢትዮጵያ ውስጥ አይሰራም፡፡ ይች ሀገር በምንሰራው ልክ ሙሉ ለሙሉ እየከፈለች ለማሰራት የምትችልበት አቅም አልደረሰችም፡፡ እንደ ሀገር ሰነድ ለሚሰጡ ተቋማት ያለው ትኩረት አነስተኛ ነው፡፡

በሪፎርም ስራው ግን ሰራተኛውን ጥቅም ለማስከበር የተጀመረ ስራ አለ፡፡ በእርግጠኝነት በቅርቡ ውጤት ላይ ይደርሳል፡፡ ቢያንስ እንኳን ደረጃቸው ሊሻሻል የሚችልበትና የሚወደው ተቋም ለማድረግ በቅርቡ አዲስ የሰራተኛና ደንብ ልብስ ይተዋወቃል፡፡ ይህም ለብሶ ለመስራት ብቻ ሳይሆን ሰራተኛው ኃላፊነት አውቆ በአግባቡ እንዲወጣ እንዲቻል ደረጃቸውን የጠበቀ ሁለት አይነት ሙሉ የደንብ ልብስ ይፋ ይደረጋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኤጀንሲው ከዚህ በፊት በ2016 በጀት ዓመት የወረቀት አገልግሎት ሙሉ በሙሉ ይቆማል የሚል መረጃ ሰጥቶ ነበር፡፡ አሁን ላይ በ15 ወረዳዎች የወረቀት አገልግሎት እየተሰጠ ነው፡፡ ለምን በእቅዱ መሰረት አልተከናወነም?**

**አቶ ዮናስ፡-** እስካሁን የተቋማችን የወሳኝ ኩነት አገልግሎት ወደ ዲጂታል ያልገባው 6 በመቶ ብቻ ነው። እነዚህ ወረዳዎች የመሰረተ ልማት እና ሌሎች ተጨማሪ ችግሮች ያሉባቸው ናቸው፡፡ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ ሲደረግ የጣት አሻራ ከሲስተሙ ጋር የሚናበበው ከአንድ የሕንድ ኩባንያ ጋር ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ሲስተሙን በኩባንያው ተቆልፏል፡፡ ይህ ማለት ድርጅቱ መጥቶ ‹‹ኢንስቶል›› ካላደረገው በቀር በራስ አቅም "ኢንስቶል"ማድረግ አይቻልም፡፡

ከድርጅቱ ጋር ቀድሞ የነበረው ውል በትብብር ነበር፤ አሁን ላይ ዶላር ካልከፈላችሁ የሚል ሀሳብ በማንሳቱ ድርድር ተደርጎ 170 የሚሆን ፈቃድ በቅርቡ ይገዛል፡፡ አሁንም እርግጠኛ መሆን የሚቻለው የወረቀት አገልግሎት በዚህ ዓመት ያበቃል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል በመሸኛ የሚመጡ ዜጎች ቁጥር ከፍተኛ ነው፡፡ ነገር ግን ከመጡ በኋላ በወረዳዎች ከሶስት እስከ ስድስት ወር ጠብቁ እየተባሉ ለተለያዩ እንግልት እየተዳረጉ ነው። አሁን ባለው ሁኔታ መታወቂያ ከሌላቸው ለችግር የሚጋለጡበት ሁኔታ ከፍተኛ ነውና ይህ እንዴት ይታያል?**

**አቶ ዮናስ፡-** እንደ ሀገር ቀድሞ ቴክኖሎጂዎችን አስገብታ ብትሰራ ኖሮ እንዲህ አይነት ችግሮች አይከሰቱም ነበር፡፡ ለመታወቂያ አሰጣጥ መሰረታዊ ችግር የሆነው ዘመናዊ የሆነ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ የአሰራር ስርዓት አለመዘርጋቱ ነው፡፡ አንድ ሰው ከተወለደ ጊዜ ጀምሮ እሱን የሚመለከት መረጃ ይቀመጣል፡፡ ይህ መረጃ እንደ ሕግ ለሁሉም መረጃ የሚያጋራ ቢኖር መሸኛ አምጥቶ አዲስ አበባ አበበ ነኝ ብሎ መዝግቡኝ ቢል ለዚህ ችግር አይዳረግም ነበር፡፡ ችግሩ ወጥ የሆነ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ አለመኖሩ ነው፡፡

አዲስ አበባ መታወቂያ አሰጣጥ የሚታገድበት አንዱ ምክንያት ሰላማዊ ያልሆኑ ሰዎች ወደ ከተማዋ በመግባት የተዛባ ማንነት ይዘው ስለሚገቡ ነው፡፡ ለምሳሌ "ዮናስ" በአንድ ክልል ነዋሪነት ተመዝግቦ መሸኛ ይዞ የአዲስ አበባ መታወቂያ ሲጠይቅ የሚያመጣው አንድ ነጠላ ወረቀት "ዮናስ" ነው ብሎ ሲሰጥ በትክክልም "ዮናስ" ስለመሆኑ የሚረጋገጥበት አንዳችም መንገድ የለም፡፡ የያዝነው ማንነት በመተማመንና በፈጣሪ ጥበቃ እንጂ ደቡብ ኦሞ ያለ አንድ የቀበሌ ሊቀመንበር የሚሰጠው የመሸኛ ወረቀት ትክክለኛ ስለመሆኑ ምንም አይነት ማረጋገጫ የለም፡፡ ይህም አዲስ አበባ ላይ ችግር ፈጥሯል፡፡ ከዚህ የተነሳ ወደ ከተማዋ የሚመጣውን ሰው ማጥራት አለብን፡፡ ከዚህ አንጻር መዝግበን የምናቆይበት ጊዜ ረዝሟል፡፡

ከሌሎች ክልሎች በመሸኛ መጥተው አዲስ አበባ ነዋሪ መሆን በግማሽ ቢዘጋም 70 በመቶው ክፍት ነው፡፡ በስራ ዝውውር፤ በሕመም አዲስ አበባ ምቹ ነው ከተባለ፤ ትምህርት ዕድል ለማግኘት አዲስ አበባ ሆኖ ለመከታተል፤ የሚፈልጉ አካላት በማስረጃ መታወቂያ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

በአንድ ቤት 20 ሰው ብቻ መታወቂያ መውሰድ ይችላል የሚለውን መመሪያ ያወጣን ስለተቸገረን ነው። በፊት በአንድ ቤት እስከ 180 ሰው ይመዘገብ ነበር፡፡ ምክንያቱም ከዚህ በፊት መመሪያው ገደብ አልነበረውም። አሁን ግን 20 ሰው የሚል ገደብ ተበጅቶለታል፡፡ ይህ ገደብ ሲመጣ ጫጫታ ተነሳ፡፡

ለምሳሌ በድሮው ኮልፌ 13 በአሁኑ አዲስ ከተማ 13 የሚኖር አንድ ሰው በውስጡ 78 ሰዎችን አስመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ ይህ ሰው መሸኛ የያዙ ሰዎችን እያመጡ መዝግቡልኝ ይላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ጌታዬ በእርስዎ ቤት 78 ሰዎች ተመዝግበዋል፡፡ እንዴት ተጨማሪ ይጠይቁናል? ተብለው በባለሙያዎች ሲጠየቁ ፤ "ምን አገባችሁ! ይህን ያህል ብቻ ነው ማስመዝገብ የሚል መመሪያ አላችሁ? አሳዩኝ!" የሚል ምላሽ ሰጡ፡፡ በእዚህ እና መሰል ችግሮችን ተከትሎ እንደመፍትሔ በአንድ ቤት ከ20 በላይ ሰዎች ማስመዝገብ አይቻልም የሚል መመሪያ ልናወጣ ተገደናል። ልጅ ከሆነ ግን 21ኛም ሆኖ መመዝግብ ይቻላል። መመሪያው ይህንን አይከለክልም፡፡ በነገራችን ላይ የዚህ መስሪያ ቤት ችግር ለዘመናት ሲንከባለል የመጣ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በበርካታ ወረዳዎች የልደት ካርድ እጥረት አለ የሚል ቅሬታ ይነሳሉ፤ እዚህ ላይ የእርስዎ ምላሽ ምንድን ነው ?**

**አቶ ዮናስ፡-** ከልደት ካርድ ተያይዞ የህትመት ችግር አለ፡፡ ችግሩን ለመፍታት ብርሃን እና ሰላም ማተሚያ ቤት ለሚያደርግልን ትብብር እውቅና እንሰጣለን፡፡ አሁን ከልደት ካርድ ጋር ተያይዞ ትልቁ ችግር የካርድ ስርጭት መሆኑን ለመግለፅ እወዳለሁ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስነበረን ቆይታ እናመሰግናለን።**

**አቶ ዮናስ፡-** እኔም መአሰግናለሁ፡፡

# ሕብረት ሥራ ማህበራቱ በወረሃ የካቲት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

በማኅበረሰቡ ዘንድ ፍትሃዊ የምርትና የሸቀጦች ስርጭት እንዲኖር በማድረግ ቀዳሚ የሆኑት ኅብረት ሥራ ማህበራት ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶችን በመስጠት ይታወቃሉ፡፡ በተለይም ሰው ተኮር በመሆናቸው ገበያን በማረጋጋት ለሸማቹ እፎይታን በመስጠት ይጠቀሳሉ፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች በግብርና ምርቶችና በመሰረታዊ ሸቀጦች ላይ የሚፈጠረውን የገበያ አለመረጋጋትና ያልተገባ የዋጋ ጭማሪን በመከላከልና ገበያን በማረጋጋት በዜጎች ላይ ሊደርስ የሚችለውን የኑሮ ጫና በማቃላል የላቀ ድርሻ አላቸው፡፡

በአገር አቀፍ ደረጃ በየዓመቱ የኅብረት ሥራ ማህበራት ኤግዚቢሽንና ባዛር የሚካሄደውም በዚሁ ምክንያት እንደሆነ ይታመናል፡፡ ዘንድሮም በአገር አቀፍ ደረጃ ለ10ኛ ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ ለ3ኛ ጊዜ «ኅብረት ሥራ ማህበራት ከገበያ በላይ ናቸው» በሚል መሪ ሃሳብ ኤግዚቢሽን፣ ባዛርና ሲምፖዚየም ተዘጋጅቷል። ኤግዚቢሽን፣ ባዛርና ሲምፖዚየሙ በአዲስ አበባ ኤግዚብሽን ማዕከል ከጥር 29 እስከ የካቲት 5 ቀን 2016 ዓ.ም ተካሂዷል፡፡ በዚሁ ኤግዚቢሽንና ባዛር ተገኝተው የተለያዩ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶቻቸውን ይዘው ለሸማቹ ያቀረቡ አምራች የኅብረት ሥራ ማህበራትና ሸማች የኅብረት ሥራ ማህበራት በርካታ ናቸው፡፡

ወረሃ የካቲትን በጉጉት የሚጠባበቀው የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪም በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል ተገኝቶ ጎብኝቷል፡፡ ጥራት ያላቸውን የአርሶ አደሩን ምርትም በተመጣጣኝ ዋጋ ሲሸምት ሰነባብቷል፡፡ ኅብረት ሥራ ማህበራቱ ይዘው የቀረቡትን የግብር እና የኢንዱስትሪ ምርቶች ሲሸምቱ ያገኘናቸው አቶ ሽፈራው አበራ ከሳሪስ አካባቢ ነው የመጡት፡፡ ባዛርና ኤግዚቢሽኑ በየዓመቱ መዘጋጀቱ መልካምና በተለይም ለአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በተወሰነ መልኩ ገበያን ማረጋጋት እንደሚችል ገልጸዋል፡፡ ለአብነትም አንድ ኪሎ ቡና በመደበኛው ገበያ ማለትም ሱቅ ላይ ከ500 እስከ 550 ብር የሚሸጥ መሆኑን ጠቅሰው በባዛርና ኤግዚቢሽኑ ጥራት ያለውን ቡና በኪሎ 350 ብር መግዛት ችለዋል፡፡

ሌሎች ምርቶችም እንዲሁ ቅናሽ ያላቸው መሆናቸውን ሲያስረዱ ጤፍ፣ ስንዴ፣ ዱቄት፣ ማርና ሌሎች ምርቶችንም ተዘዋውረው የተመለከቱ ሲሆን፤ በሁሉም የምርት አይነቶች ከመደበኛው ገበያ ቅናሽ መኖሩን አመላክተዋል፡፡ ከግብርና ምርቶች በተጨማሪም የኢንዱስትሪ ምርቶች ፓስታ፣ ማካሮኒ፣ ዘይትና የጽዳት ዕቃዎች ላይም መጠነኛ የሆነ ቅናሽ መታየቱን ነው ያመላከቱት፡፡

ኤግዚቢሽንና ባዛሩ በየዓመቱ መዘጋጀቱ እጅግ በጣም ጥሩና ገበያውን በማረጋጋት የበኩሉን ድርሻ መወጣት መቻሉን ያነሱት አቶ ሽፈራው፤ የዘንድሮ ባዛርና ኤግዚቢሽን እንደ ከዚህ ቀደሞቹ ሞቅ ያለ አለመሆኑን ነው የታዘቡት፡፡ እሳቸው እንዳሉት ከዚህ ቀደም በርካታ ቁጥር ያለው ሸማች ተገኝቶ በስፋት ይሸምት ነበር፡፡ አሁን ላይ ግን ምርት አለ የሸማች ቁጥር ግን ቀንሷል ነው ያሉት፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የኑሮ መወደድና የዋጋ ንረቱ እንዲሁም የቦታው ርቀት ሳይሆን እንዳልቀረ ነው ያስረዱት፡፡

ሌላኛዋ ሸማች ወይዘሪት ንጋቷ ቦጋለ ትባላለች። ከየካ ክፍለ ከተማ ከወረዳ አስር የመጣችው ንጋቷ፤ በባዛርና ኤግዚቢሽኑ የቀረቡ ምርቶች በርካታ እንደሆኑ ጠቅሳ፤ ሸማቹ ምርቶቹን በቀጥታ ከገበሬው መሸመት መቻሉ አሁን ያለውን የኑሮ ውድነት በከፊል ማረጋጋት የሚችል እንደሆነ ትናገራለች፡፡

እሷ እንዳለችው የአትክልትና ፍራፍሬ ዋጋ በተለይም ሽንኩርት እጅግ በጣም መወደዱ ይታወቃል። በባዛርና ኤግዚቢሽኑ ደግሞ ሽንኩርትን ጨምሮ የተለያዩ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም ጤፍ፣ ስንዴ፣ በቆሎና ሌሎች ምርቶችም ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ምርቶችም በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማቹ እየቀረቡ ነው፡፡

ሽንኩርት ውጭ ላይ ካለው ዋጋ ተመጣጣኝ እንደሆነና በኪሎ ከ80 እስከ 90 ብር መግዛቷን ገልጻለች፡፡ ቲማቲምም እንዲሁ ውጭ ካለው ገበያ በብዙ እጥፍ የሚቀንስ መሆኑን ጠቅሳ በኪሎ ስምንት ብር መግዛቷን ተናግራለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ማር በመደበኛው ገበያ በኪሎ እስከ ስድስት መቶ ብር ሲሆን በባዛርና ኤግዚቢሽኑ ንጹህ የአርሶ አደሩን ማር በኪሎ ከ300 እስከ 350 ብር እየተሸጠ ስለመሆኑ አስረድታለች፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ገበያን በማረጋጋት ትልቅ ድርሻ ያላቸው መሆኑን ያነሳችው ንጋቷ፤ ባዛርና ኤግዚቢሽኑ ዓመት ጠብቆ ከሚዘጋጅ ይልቅ በዓመት ሁለትና ሶስት ጊዜ መዘጋጀት ቢችል ማኅበረሰቡን አሁን ካለው የኑሮ ጫና ማገገዝ እንደሚቻል ስትገልጽ፤ በተለይም ቦታው መሀል ከተማ እንደመሆኑ በከተማ ዳርቻ ራቅ ባሉ አካባቢዎች ለሚገኘው ሸማች በአቅራቢያው ተደራሽ መሆን እንዲችል ቢደረግ መልካም እንደሆነ በመግለጽ ሀሳቧን ቋጭታለች፡፡

ኤግዚቢሽን፣ ባዛርና ሲምፖዚየሙ አምራች የኅብረት ሥራ ማህበራትንና ሸማች የኅብረት ሥራ ማህበራትን ማገናኘት ዋና ዓላማቸው ሲሆን፤ የባዛርና ኤግዚቢሽኑ በተለይም የኅብረት ሥራ ማህበራትን ከተጠቃሚው ጋር በቀጥታ ማገናኘትና ማስተዋወቅ ዋነኛ ተግባሩ ነው፡፡ ከዚህም ባለፈ ሸማቹ ምርቶቹን መሸመት እንዲችልና አምራቹም ምርቱን መሸጥ የሚችልበት የተሳለጠ መድረክ ነው፡፡ ሌላው መድረኩ ዘላቂ የሆነ ትስስር መፍጠር ያለመ ሲሆን፤ አምራች የኅብረት ሥራ ማህበራትና ሸማች የኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲሁም ሸማቾች ዘላቂ የገበያ ትስስር እንዲፈጥሩ በማስቻል የኅብረት ሥራ ማህበራቱ ገጽታቸውን መገንባት የቻሉበት አጋጣሚ መሆኑ ተገልጿል፡፡

በአገሪቱ የሚገኙ ከ110 ሺ በላይ የሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲሁም ዩኒየኖች መኖራቸውን የጠቀሱት የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጌታቸው መለሰ (ዶ/ር) እንዳሉት እነዚህ ኅብረት ሥራ ማህበራት በአንድ መድረክ ተገናኝተዋል፡፡ በመሆኑም ዩኒየኖቹ ገጽታቸውን መገንባት ችለዋል፡፡ መድረኩ ዘርፉ በአገር አቀፍ ደረጃ እያበረከተ ያለውን ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ምን እንደሚመስል ማስተዋወቅ የቻለ ነው፡፡

ማኅበራቱ እሳስካሁን ባላቸው አገራዊ ነባራዊ ሁኔታ 18 በመቶ የገበያ ድርሻ ያላቸው እንደሆኑም ኮሚሽነሩ ተናግረዋል፡፡ በቀጣይም ከዚህ የበለጠ የገበያ ድርሻ እንዲኖራቸው የሚፈለግ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ ለዚህም፤ ኤግዚቢሽንና ባዛር አንዱና ዋናው መንገድ መሆኑን ጠቅሰው፣ በዚህ መድረክ ዘላቂ የገበያ ትስስር መፍጠር እንደተቻለ ነው የተናሩት፡፡ ባዛርና ኤግዚቢሽን በሚካሄድበት ወቅት ሸማቹ ኅብረተሰብ ወይም የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት ጊዜ ወስደው ከኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ቀጣይነት ያለው የገበያ ትስስር እንዲፈጥሩ የሚያስችል መሆኑን ገልጸው፣ ይህም በመሀል ያለውን ረጅም ሰንሰለት በማሳጠር ደላሎችን በማስወጣት በግብይት ሂደት ውስጥ የሚፈጠረውን ውጣ ውረድ ለማሳጣር እንደሚጠቅም ተናግረዋል፡፡

በተጨማሪም የኢንዱስትሪ አምራቾች፣ የፋይናንስ ተቋማት፣ የፖሊሲ አውጪዎችና ምሁራንም ጭምር ከኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር መገናኘት አለባቸው ያሉት ኮሚሽነሩ፤ በባዛርና ኤግዚቢሽኑ ከሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች የሚመጡ የኅብረት ሥራ ማህበራት እርስ በእርስ የልምድ ልውውጥ የሚያደርጉበትና በርካታ ተግባራ የሚከናወኑበት ኤግዚቢሽንና ባዛር መሆኑን አመላክተዋል፡፡

**በአገሪቱ ያለው የንግድ ስርዓት እጅግ የተወሳሰበና ሰንሰለቱ የረዘመ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በርካታ ችግሮች የሚስተዋሉበት በመሆኑ ይህን ችግር ለመቅረፍ የኅብረት ሥራ ማህበራት የመፍትሔው አካል መሆን ይችላሉ**

በአገሪቱ ያለው የንግድ ስርዓት እጅግ የተወሳሰበና ሰንሰለቱ የረዘመ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በርካታ ችግሮች የሚስተዋሉበት በመሆኑ ይህን ችግር ለመቅረፍ የኅብረት ሥራ ማህበራት የመፍትሔው አካል መሆን ይችላሉ። አጠቃላይ በግብይት ስርዓቱ የሚስተዋሉ ችግሮችን ሙሉ ለሙሉ ኅብረት ሥራ ማህበራቱ ይቀርፋሉ ተብሎ የሚታሰብ ባይሆንም የበኩላቸውን አበርክቶ እየተወጡ እንደሆነ ያላቸውን ዕምነት የገለጹት ኮሚሽነሩ፤

ኅብረት ሥራ ማህበራት ከሌላው የንግዱ ማህበረሰብ ይልቅ ሰው ተኮር እንደሆኑ ገልጸው በተጠቀሰው ጊዜ ለሸማቹ ማህበረሰብ ምርቶቻቸውን በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ እንደቻሉ አስረድተዋል፡፡ ባዛርና ኤግዚቢሽኑ በአገር አቀፍ ደረጃ በየዓመቱ የሚዘጋጀውም በዚሁ ምክንያት እንደሆነ ጠቅሰው፤ ከሌሎችም በአገር አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጀውን ባዛርና ኤግዚቢሽን ተከትለው በየደረጃው እንደሚያዘጋጁም አመላክተዋል፡፡ በዚህም ኅብረት ሥራ ማህበራቱ ገበያን በማረጋጋት የበኩላቸውን እየተወጡ እንደሆነ ነው ያስረዱት፡፡

ኮሚሽነሩ እንዳብራሩት፤ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዘርፈ ብዙ አገራዊ ሚና ያላቸው ሕዝባዊ ተቋማት ናቸው፤ ማኅበራቱ ከግብይት ባለፈ የገንዘብ ቁጠባና ብድር፣ የቤቶች የኅብረት ሥራ ማህበራት፣ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራትና የአምራቾች ኅብረት ሥራ ማህበራትም አላቸው፡፡ ሁሉም በማህበረሰብ ውስጥ ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶችን እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ ዘንድሮ የተካሄደው ኤግዚቢሽንና ባዛርም «ኅብረት ሥራ ማህበራት ከገበያ በላይ ናቸው» በሚል መሪ ሃሳብ መሆኑ በዚሁ ምክንያት ነው ብለዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ማህበራት የተደራጀ ማህበረሰብ ያላቸውና በስራቸው 28 ሚሊዮን የሚደርስ ሕዝብ ያላቸው በመሆናቸው አገልግሎታቸውም ዘርፈ ብዙ ነው፡፡ በተለይም አገሪቱ ለምትከተለው አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ አቅጣጫ ትልቅ ድርሻ ያላቸውና ሰፊውን የገጠር ሕዝብ በመድረስ የአገሪቱን ብልጽግና ለማረጋገጥም ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ ናቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም የኑሮ ጫናን በማቃለል በተለይም የአዲስ አበባ ከተማ ሸማች ማህበረሰብ ከኅብረት ሥራ ማህበራት ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘት የሚችልበትን ዕድል መፍጠር የቻሉና በየዓመቱ በወረሃ የካቲት የሚጠበቁ እንደሆኑ በመግለጽ በቀጣይም ተጠናክረው የሚቀጥሉ እንደሆነ አመላክተዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነር ወይዘሮ ልዕልቲ ግደይ በበኩላቸው እንዳሉት፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለኤግዚቢሽንና ባዛሩ መሳካት ወራትን የወሰዱ በርካታ ሥራዎችን ሲሰራ መቆየቱን ሲያስረዱ፤

አዲስ አበባ የግብርና ምርቶችን የማታመርት በመሆኑ ለባዛሩ አስፈላጊ የሆኑ ምርቶች ወደ ባዛርና ኤግዚቢሽኑ እንዲሁም ወደ ከተማዋ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ከአምራች ክልሎች ጋር ምርት የማፈላለግና ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ትስስር በመፍጠር ምርቶቹ ወደ ከተማዋ መግባት የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ ከግብርና ምርቶች ባሻገርም ከትላልቅ የፋብሪካ ባለቤቶች ጋር በጋራ በመሆን የተለያዩ የኢንዱስትሪ ምርቶች ወደ ኤግዚቢሽንና ባዛሩ እንዲገቡ የተለያዩ ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡ በዚህም የኅብረት ሥራ ማህበራት ለሸማች ማህበራት ምርቶችን በበቂ ሁኔታ አሰባስቦ ለግብይቱ ማቅረብ ተችሏል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ከስምንት ሺ በላይ የኅብረት ሥራ ማህበራት መኖራቸውን የጠቀሱት ወይዘሮ ልዕልቲ፤ ከእነዚህም ውስጥ 154 ሸማች የኅብረት ሥራ መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡ 1600ዎቹ ደግሞ የቁጠባ ማህበራት እንደሆኑ ጠቅሰው፣ ሌሎች ማኅበራት እንዳሉም ተናግረዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል ከ125 በላይ የሚሆኑ ልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰጡ አምራቾችና የኅብረት ሥራ ማህበራት ምርትና አገልግሎታቸውን ለከተማው ነዋሪ ማቅረብ ችለዋል፡፡

ከ88 በላይ የሚሆኑ የሸማች ኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶቻቸውን ይዘው የቀረቡ ሲሆን፤ ምርቶቹም እሴት የተጨመረባቸውና ጥራት ያላቸው ናቸው፡፡ በሚፈለገው መጠን የሚቀርብበት ምቹ ሁኔታም ተፈጥሯል፡፡ ሸማቹም የሚፈልገውን ምርት በሚፈልገው መጠን በተመጣጣኝ ዋጋ መሸመት እንደቻለ ያላቸውን ዕምነት ገልጸዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ላለፉት ሁለት ዓመታት በሌማት ትሩፋት እንቅስቃሴው በከተማ ላይ ትርጉም ያለው ሥራ መስራቱንና ለውጥ ማምጣቱን ጠቅሰው፤ በተለይም በዶሮና በከብት እርባታ ውጤት መመዝገቡን አስታውቀዋል። በዚህ ዘርፍ የተሰማሩ ማህበራት የራሳቸውንና የአካባቢያቸውን ፍላጎት ከማሟላት ባሻገር የማምረት አቅማቸውን በማሳደግ ትላልቅና አገር አቀፍ በሆኑ ባዛርና ኤግዚቢሽኖች በመሳተፍ ምርቶቻቸውን ለሕዝቡ ይዘው መቅረብ እንደቻሉም አስገንዝበዋል፡፡

ከስድስት በላይ የሚሆኑ የፋብሪካ ባለቤቶችም እንዲሁ የኢንዱስትሪ ምርቶቻቸውን ይዘው መቅረባቸውን ያነሱት ኮሚሽነሯ፤ ዘይት፣ ፓስታ ማካሮኒና ዱቄት የመሳሰሉ የምግብ ሸቀጦችንና የጽዳት ዕቃዎች ለሸማቹ ማህበረሰብ በተመጣጣኝ ዋጋ ቀርበዋል፡፡ በባዛርና ኤግዚቢሽኑ ላይ የተለያዩ የግብርና እንዲሁም የኢንዱስትሪ ምርቶችን ከመሸጥ ባለፈ በቀጣይነት ምርቶችን ለከተማው ነዋሪ ማቅረብ የሚቻልበትን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር በተለይም ከክልል ከሚመጡ አምራቾች ጋር ትስስር በመፍጠር ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ተጨማሪ የምርትና የገበያ ትስስር መፍጠር የሚችል እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

የዘንድሮው ኤግዚቢሽንና ባዛር የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ከአዲስ አበባ ከተማ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በጋራ የተዘጋጀ ሲሆን፤ ይህ በመሆኑም ባለፉት ዓመታት ከተካሄዱት ኤግዚቢሽንና ባዛሮች የተለየ እንዲሆን አድርጎታል ነው የተባለው፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## የ‹‹ሿሿ›› ዘመቻ

**ዋለልኝ አየለ**

አንዳንድ ምኞቶች ወይም ‹‹እንዲህ ቢደረግ›› ብለን ያሰብናቸው ነገሮች ተሳክተው ሲታይ ደስ ይላል፡፡ ከዓመት ፊት ይመስለኛል፤ በተለምዶ ‹‹ሿሿ›› እየተባለ ስለሚጠራው የስርቆት አይነት አንድ ትዝብት እዚሁ ገጽ ላይ አስነብቤ ነበር፡፡ ጥቅል ሀሳቡ፤ ፖሊስ የሆነ የመጠቆሚያ አድራሻ ሰጥቶ ቢሰራበት የሚል ነበር፡፡ ሰዎች አጠራጣሪ ምልክት ሲያዩ ወይም የዚህ ስርቆት ሰለባ ሲሆኑ ወዲያውኑ ተሽከርካሪውን ማስያዝ የሚችሉበት አጋጣሚ ቢኖር የሚል ነበር፡፡ ይህን ለማድረግ የፀጥታ አካል የጥሪ ማዕከል ቢኖር የሚል ነበር፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአዲስ አበባ ፖሊስ በተደጋጋሚ የሚወጡ ዜናዎች ያንን ምኞቴን አስታወሱኝ፡፡ ሰሞኑን ልብ ብላችሁ ከሆነ ፖሊስ በተከታታይ የሚለቀው ዜና በተለምዶ ‹‹ሿሿ›› የሚባለውን የስርቆት አይነት የፈጸሙ ሰዎችን የሚያጋልጥ ነው፡፡ የሰረቁትን ንብረት (በዋናነት ሞባይል ስልክ) እና የሌቦችን ምስል በግልጽ በማሳየት መቀጣጫ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡ ከማስፈራራት ባለፈ በተግባር ተደረገ ማለት ነው፡፡ ይህ የአንድ እና የሁለት ቀን አጋጣሚ ብቻ አይደለም፤ እስከ ቅርብ ቀናት ድረስ የሰማነው ዜና ነው፡፡ ፖሊስ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራበት ነው ማለት ነው፡፡

በነገራችን ላይ ፖሊስ ከፍተኛ ዘመቻ የሚጠበቅበት ለጥቂት ጊዜያት ብቻ ነው፤ ከዚያ በኋላ ጭራሹንም ይጠፋሉ፡፡ ምክንያቱም እንደማይሳካ እና እንደማይቻል አወቁት፡፡ ይህ ማለት ፖሊስ አርፎ ይቀመጥ ማለቴ አይደለም፤ ዳሩ ግን ሌሎች ይጠፋሉ። ከቅርብ ቀናት ወዲህ በተከታታይ የሚሰሙት ዜናዎች የስርቆት ወንጀል የፈጸሙ ሰዎች ምስላቸው በማህበራዊ መገናኛ ዘዴዎች ሲዘዋወር ነው፡፡ ይህ ፎቶ ወላጆቻቸውና ዘመድ አዝማድ ያየዋል፡፡ ‹‹የእገሌ ልጅ ሰርቆ ተያዘ›› መባል በባህላችን እጅግ በጣም ነውር ነው፡፡ እነዚህ ወጣቶች ምስላቸው ሲዘዋወር ስለነበር የትኛውም ቦታ ቢሄዱ በሌብነት ነው የሚታወቁት። ከአንድ ቦታ የሰረቁትን ንብረት ሸጠው ሌላ ቦታ ሲዝናኑበት ቆይተዋል፡፡ አሁን ግን እንዲህ አይነት ወጣቶች ሲዝናኑ የተመለከተ ሁሉ ‹‹እነዚህ ሌቦች›› ይላል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ይህን ውርደት በመፍራት ከዚህ በኋላ ስርቆትን እንደ አማራጭ የሚሞክር አይኖርም፡፡

አይኖርም ብለን እንዘናጋ ማለት አይደለም፤ ፖሊስም ክትትሉን ያቁም ማለት አይደለም፡፡ ዳሩ ግን አሁን ላይ እየተደረገ ያለው ይህ የ‹‹ሿሿ›› የክትትል ዘመቻ እጅግ ሊመሰገን የሚገባ እና ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት የሚችል ነው፡፡ በፖሊስ ባህል አንድ አሰራር አለ፡፡ ‹‹ፓትሮል›› የሚባለው ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ፖሊስ በአንድ አካባቢ እየዞረ መታየት ማለት ነው፡፡ ፖሊስ በዚያ አካባቢ ሲዞር ታየ ማለት በአካባቢው አለ ማለት ነው፡፡ ይህ ለዜጎች ምን ያህል ሰላምና መረጋጋት እንደሚፈጥር፣ ለሌቦች ደግሞ ምን ያህል የስርቆት ተስፋ መቁረጥ እንደሚፈጥር ከተጨባጭ ማሳያዎች ማየት እንችላለን፡፡

በአካባቢያችሁ ስርቆት ባይሆን እንኳን የሆነ ህጋዊ ያልሆነ ነገር ለማድረግ ያሰቡ ሰዎን ልብ በሉ፡፡ ለምሳሌ፤ በህገ ወጥ መንገድ የሚሸጥ ነገር አለ እንበል። እነዚህ ሰዎች ምን ሲሉ ትሰማላችሁ? ከወዲያኛው አካባቢ የሚመጣውን ሰው ‹‹እኔ እምልህ? እዚያ ጋ ስትመጣ ፖሊሶች አሉ እንዴ?›› ብለው ይጠይቃሉ። ‹‹አዎ›› ብሎ ከመለሰ ተስፋ ቆረጡ ማለት ነው፡፡ ፖሊስ በአካባቢው አለ ማለት ይደረስብናል ብለው ይፈራሉ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ፖሊስ አለ ሲባል የግድ በእያንዳንዱ ግቢ በር ላይ አለ ማለት አይደለም፤ በአካባቢው ካለ ሌቦች ይፈራሉ፡፡ ስለዚህ ‹‹ፓትሮል›› የሚደረገው በአካባቢው አለን ለማለት ነው፡፡

ይህ አሁን የተጀመረው የ‹‹ሿሿ›› ሌቦችን የማደን ዘመቻ ልክ እንደ ‹‹ፓትሮል›› ማለት ነው። ከዚህ በኋላ አታመልጡም ማለት ነው፡፡ ‹‹አሁን ሲሰለቻቸው ይተውታል›› ብሎ የሚገባበት ሌባ ካለ ራሱንም ቤተሰቡንም ውርደት ላይ ይጥላል ማለት ነው፡፡ ይህኛውን ወንጀል እጅግ የከፋ የሚያደርገው መታሰሩ ብቻ አይደለም፡፡ ምስሉ በማህበራዊ ገጾች እና በቴሌቪዥን ጣቢያዎች ላይ እንዲታይ ይደረጋል። ይህ ሰው በሄደበት ሁሉ አንገቱን ደፍቶ ይኖራል ማለት ነው፡፡ ቀና ብሎ የመኖር ሞራል አይኖረውም። ታማኝነት የለውም፤ ይህ ሰው ታማኝነት የለውም ማለት ምንም አይነት ሥራ እንኳን አምኖ የሚያሰራው አይኖርም ማለት ነው፡፡ ዕድሜ ዘመኑን በሥርቆት ሊኖር አይችልም፡፡ ስለዚህ ሰርቶ መብላት እንኳን የማይችልበትን ሁኔታ እየፈጠረ ነው፡፡

በነገራችን ላይ የ‹‹ሿሿ›› ሌቦች የዕለት ጉርስ የቸገራቸው ናቸው የሚባሉ እንኳን አይደሉም፡፡ ሰርተው መብላት የሚችሉ ወጠምሻ ጎረምሶች ናቸው። ምቹ አጋጣሚ ካገኙ ሰዎችን በሃይል (በድብደባ) የሚነጥቁ ናቸው፡፡ ስልኩን ከኪሱ ሲያወጡ የደረሰባቸው ሰው ግብ ግብ ቢገጥም ለመደባደብ የተዘጋጁ ጡንቸኞች ናቸው፡፡ ስለዚህ ወንበዴዎች ናቸው፡፡ እንኳን ምስላቸውን ማሳየት ቢገረፉ ራሱ አያሳዝኑም፤ ምክንያቱም ጨለማን ተገን አድርገው የስንቱን አንገት የቆለመሙ ናቸው፤ የስንቱን ሕይወት የቀጠፉ ናቸው፡፡

እነዚህ ሰዎች ለአገር የሚጠቅም የፈጠራ ሥራ በመስሪያ ዕድሜያቸው የድሃ ንብረት እንዴት እንደሚዘርፉ ነው ሲያውጠነጥኑ የሚውሉት፡፡ ሀገር የሚገነባ ጉልበታቸውን የሰው አንገት ለመቆልመም ተጠቀሙበት፡፡ ስለዚህ እንዲህ አይነት ወንበዴዎችን ለመቆጣጠር ማንም ሰው ተባባሪ እና ጠቋሚ ሊሆን ይገባል፡፡

እንኳን በተጨባጭ በምስል ማስረጃ የተያዙ ሰዎችን አሳይተው፤ ማስፈራሪያ ማድረግ በራሱ ዋጋ አለው፡፡ በሌቦች ላይ ፍርሃት ይፈጥራል፡፡ ፖሊስ ‹‹ፓትሮል›› ሲያደርግ ጥይት እየተኮሰ እና ሰዎችን እየገረፈ አይደለም፡፡ እንደማንኛውም መንገደኛ ነው የሚሄድ፤ ዳሩ ግን የፀጥታ አስከባሪ ስለሆነ ለምን ዓላማ እንደሚንቀሳቀስ ስለሚታወቅ ሌባ በዚያ አካባቢ ዝር አይልም ማለት ነው፡፡

የ‹‹ሿሿ›› ሌቦች ላይ የሚሰራው ተከታታይ ዘገባ ራሱን የቻለ ሌባን የማጽዳት ዘመቻ አካል ነው፡፡ በአንድ በኩል ራሳቸው ሌቦች ከፖሊስ እንደማያመልጡ ስለሚያውቁ ከድርጊታቸው ይቆጠባሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝቡ ለፖሊስ መጠቆምን እና አጠራጣሪ ነገር ሲያይ ለፀጥታ አካላት አሳልፎ መስጠትን ባህል ያደርገዋል፡፡ እስከ ዛሬ የምናየው ወቀሳ ብቻ ነበር። ሕዝቡ ራሱ ‹‹ብንናገርም መፍትሔ አይመጣም›› በሚል ሰበብ አጠራጣሪ ነገሮችን የማጋለጥ ልማድ አልነበረውም፡፡ አሁን ግን ለውጡን በተጨባጭ ሲያይ ለመጠቆም ይነሳሳል፡፡

በእንዲህ አይነት የጋራ ደህንነትን በሚያውኩ ድርጊቶች እና የሰዎችን ገንዘብና ሕይወት በሚቀጥፉ ሌቦች ላይ ፖሊስና ሕብረተሰብ የጋራ ትብብር ሊያደርግ ይገባል፡፡ የፀጥታ አካላት በሚሰጧቸው የመጠቆሚያ አድራሻዎች የመጠቆም እና እኛም የጋራ ደህንነቱ አካል መሆን ይልመድብን!

# ዓለም አቀፍ

## አውሮፓ ሙሉ በሙሉ ራሷን የመከላከል አቅም ለማዳበር 10 ዓመት ያስፈልጋታል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አውሮፓ ሙሉ በሙሉ በወታደራዊ ጉዳዮች ራሷን የመከላከል አቅም ለማዳበር 10 ዓመት እንደሚያስፈልጋት ግዙፉ የጀርመን የመከላከያ ኩባንያ የሆነው ርሄይንሜታል ኃላፊ ለቢቢሲ ተናገሩ።

የአህጉሪቱ የጦር መሳሪያ ክምችት “መመናመኑንም” ነው አርሚን ፓፐርገር የተናገሩት። ኃላፊው ይህንን አስተያየት የሰጡት የጀርመኑ ቻንስለር ኦላፍ ሾልዝ ግዙፍ የተባለውን የጦር መሳሪያ ማምረቻ ኩባንያ የመሰረት ድንጋይ ለመጣል ሎወር ሳክሶኒ በተባለችው ግዛት በተገኙበት ወቅት ነው።

በዚህ ዝግጅት ላይ የጀርመን የመከላከያ ሚኒስትር ቦሪስ ፒስቶሪየስ እና የሆላንድ ጠቅላይ ሚኒስትር ሜቴ ፍሬደሪክሰንም ተገኝተው ነበር።

ለዚህ ሁሉ የጦር መሳሪያ ክምችት “መመናመን” ስጋት መነሻ የሆነው የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ ከቀናት በፊት የሰጡት አስተያየት ነው።

በመጪው የአሜሪካ ምርጫ የሪፐብሊካኑ ቀዳሚ እጩ የሆኑት ዶናልድ ትራምፕ የሰሜን አትላንቲክ ጦር ቃል ኪዳን ድርጅት (ኔቶ) አባል አገራት የሚጠበቅባቸውን መዋጮ ባለመክፈላቸው አገራቸው ከየትኛውም ወረራ እንደማትከላከልላቸው ለአንድ መሪ መንገራቸውን አስረድተዋል።

በአወዛጋቢ ንግግሮቻቸው የሚታወቁት ትራምፕ በነዚህ አገራት ላይ ወራሪዎች የፈለጉትንም እንዲያደርጉ “እንደሚያበረታቱም” አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

ርሄይንሜታል በአዲሱ የጦር መሳሪያ ማምረቻ ላይ ከ300 ሚሊዮን ዶላር በላይ መዋዕለ ንዋይ እንደሚያፈስም አስታውቋል። ማምረቻው በየዓመቱ 200 ሺህ የሚሆኑ የከባድ መሳሪያ ጥይቶችን እንደሚያመርትም ተነግሯል።

ሆኖም “ኔቶን መዋጋት የሚፈልግ ወራሪ ከመጣ” ለጦር ዝግጅት ረዘም ያለ ጊዜ እንደሚያስፈልግ ነው የገለጹት። “በሦስት፣ አራት ዓመታት ጥሩ እንሆናል። ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ለመዘጋጀት አስር ዓመት ያስፈልገናል” ብለዋል።

“በአውሮፓ በየዓመቱ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ጥይቶች ማምረት ይጠበቅብናል” ሲሉም ነው ኃላፊው ያስረዱት። አውሮፓ የነበራት የጦር መሳሪያ ክምችት ዩክሬንን ለማገዝ የሄደ ሲሆን “ይህም የአገሪቱን ክምችት አመንምኖታል” ብለዋል።

“ጦርነት እስከቀጠለ ድረስ ዩክሬንን ልናግዝ ይገባል፤ ነገር ግን የሚያስፈልገንን የጦር መሳሪያ ክምችት ለመሙላት ቢያንስ አምስት ዓመት ሙሉ ለሙሉ ለመዘጋጀት ደግሞ አስር ዓመት ያስፈልገናል” ሲሉም አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

በተያያዘ የአሜሪካ መከላከያ ሚኒስትር ሎይድ ኦስቲን በወራት ውስጥ ለሦስተኛ ጊዜ ሆስፒታል በመግባታቸው ለሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃል ኪዳን ድርጅት (ኔቶ) ስብሰባ የሚያደርጉትን ጉዞ ሰርዘዋል።

የ70 ዓመቱ ኦስቲን ባጋጠማቸው ህመም ምክንያት በዋሽንግተን ዲሲ በሚገኝ ሆስፒታል ጥብቅ የሕክምና ክትትል በሚያስፈልጋቸው ህሙማን ክፍል ውስጥ ናቸው። ፔንታገን እንዳለው ሚኒስትሩ ሆስፒታል የገቡት ድንገተኛ የሽንት ፊኛ ችግር ገጥሟቸው ነው።

ኦስቲን ያለፈው ማክሰኞ ወደ ሥራቸው እንደሚመለሱ ተስፋ እንዳለው ፔንታገን የገለጸ ሲሆን ለጊዜው ግን ያለባቸው ኃላፊነት ለምክትላቸው ተላልፏል ብሏል።

የዋልተር ሪድ የጦር ሆስፒታል ባለሥልጣናት መግለጫ እንዳለው ሚኒስትሩ ለተራዘመ ጊዜ ሆስፒታል ውስጥ ይቆያሉ ተብሎ አይጠበቅም። “ሚኒስትሩ በቅርቡ ወደ መደበኛ ሥራቸው እንደሚመለሱ ተስፋ አለን” ብሏል መግለጫው።

ሆኖም የመጀመሪያ ጥቁር የአሜሪካ መከላከያ ሚኒስትር ሆስፒታል ውስጥ የሚቆዩት ለምን ያህል ጊዜ



እንደሆነ አልተጠቀሰም።

አሁን ላይ ኦስቲን ያጋጠማቸው የሽንት ፊኛ ችግር ከካንሰር እንደሚያገግሙ የተጣለውን ተስፋ እንደማይለውጥም ተነግሯል።

የፔንታገን ቃል አቀባይ ሜጀር ጀነራል ፓት ራይደር እንዳሉት “ኦስቲን እያደረጉ ያለው የካንሰር ሕክምና አመርቂ ውጤት እያስገኘ ነው”

ሚኒስትሩ በቤልጂየም ብራስልስ በዩክሬን ዲፌንስ ኮንታክት ግሩፕ (ዩዲሲጂ) ስብሰባን ይመራሉ ተብሎ ተጠብቆ ነበር። ይህ ጉዟቸው ቢሳካ ሆስፒታል ከገቡ በኋላ የሚያደርጉት የመጀመሪያው የባህር ማዶ ጉዞ ይሆን ነበር።

ከዚህም በተጨማሪ ሐሙስ ዕለት በሚካሄደውና በሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃል ኪዳን ድርጅት (ኔቶ) ኃላፊ ጀንስ ስቶልትንበርግ በሚመራው የድርጅቱ መከላከያ ሚኒስትሮች ስብሰባ ላይ ለመገኘትም ይዘውት የነበረው እቅድ ሳይሳካ ቀርቷል።

ኦስቲን ዩክሬንን ለመከላከል የተቋቋመው ቡድን የመጨረሻ ስብሰባ ላይ የተካፈሉት ጥር ወር መጨረሻ ላይ ከቤታቸው ሆነው ነበር። አሁንም የቡድኑን ስብሰባ ላይ በበይነ መረብ አማካኝነት ለመካፈል ማቀዳቸውንም ቢሯቸው ለቢቢሲ ገልጿል።

ሚኒስትሩ ታኅሳስ ወር ላይ የፕሮስቴት ካንሰር ሕክምና ሲያደርጉም ሆነ ጥር ወር ላይ በድጋሚ ወደ ሆስፒታል ሲሄዱ ለሕዝቡም ሆነ ለአሜሪካ የመንግሥት መዋቅር ላይ ላሉ ቁልፍ ሰዎች አለማሳወቃቸውን ተከትሎ ምርመራ እየተካሄደባቸው ነው።

## ነፃ ሃሳብ

# የእናት አፍሪካ ተስፋና...

ከ ገጽ 5 የዞረ

(ከፌብሯሪ 17 እስከ 18 2024 የሚካሄደው) የአህጉሪቱ መሪዎች ጉባኤ ቀዳሚ የመወያያ አጀንዳዎችም peace and security, regional integration, እና development ተብለው ተቀምጠዋል። እንደ አህጉር፣ ለእነዚህ ችግሮች መፍትሄን ለመሻት ደግሞ ከአፍሪካ ሕብረት የመሪዎች ጉባኤ የተሻለ መድረክ የለም።

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (አሁን የአፍሪካ ሕብረት) የተመሰረተበትን ግንቦት 17 ቀን 1955 ዓ.ም ለማሰብ፤ አፍሪካ ብዙ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ተሻግራ የመጣች መሆኗን፤ ለሁሉም ልጆቿ ፍትህ እና ሰላም ለማረጋገጥ ምን ያህል ተጨማሪ ሥራ መሰራት እንዳለበት ለመገንዘብና ለማስገንዘብ በማሰብ "የአፍሪካ ቀን ን" የምታከብረው እናት አፍሪካ በአህጉሪቱ ውስጥ፤ እንዲሁም በዓለም ምጣኔ ሃብታዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታ ወሳኝ ሚና ያላት መሆኑ በሚገባ ተረጋግጧል።

የአፍሪካ ቀንድ ከመካከለኛው ምሥራቅ እና ከባሕረ ሰላጤው አገራት ነዳጅ እና ከእስያ ደግሞ ወሳኝ የኢንዱስትሪ ምርቶች ሰፊ ተጠቃሚ ወዳለባቸው የአውሮፓ እንዲሁም የአሜሪካ አህጉር የሚተላለፍበት ቁልፉ የቀይ ባሕር መተላለፊያ ስፍራን ለመቆጣጠር ካለፉት ዘመናት ጀምሮ፣ ኃያላን አገራቱ ተጽእኗቸውን እና ቁጥጥራቸውን ለማጠናከር በስፋት እየተንቀሳቀሱ ነው።

ምንም እንኳን አሁን ላይ "ለአፍሪካ ችግር አፍሪካዊ መፍትሄ" ቢባልም የአፍሪካን ችግሮች ለመፍታት እንደ ውሀ ቀጂ የሚመላለሱት እነ እንቶኔ እንጂ ሌሎች አይደሉም። ከአፍሪካ ሕብረት ይልቅ የአውሮፓ ሕብረት ነው "በአፍሪካ ላይ ያገባኛል" ሲል የሚሰማው። ይህ ደግሞ የእናት አፍሪካ አንዱና ቁልፍ ችግር ነው።

የዚህ ቀጣና ችግር ሁሌም ሲነሳና ሲጣል ይኑር እንጂ "የችግሩ ምንጭ ምንድን ነው፣ የግጭቶቹ ዘዋሪስ ማን ነው፤ ከግጭቶቹስ አትራፊው የሚል ማን ነው?" ለሚለው እስካሁን ደፍሮ መልስ የሰጠ ማንም የለም። "አለ" ከተባለም እርስ በእርስ ጣት ከመጠቋቆም ያለፈ አይደለም። በመሆኑም፣ ሁሉም እንደ ቀጠለ ነው።

የኃያላኑ ዐይን በአፍሪካ ቀንድ ላይ ማፍጠጡን በተመለከተ ዘገባዎች ለንባብ ያልበቁበት ጊዜ አለ ለማለት የሚደፍር የለም። ያልተደረጉ ጥናቶች አሉ ለማለት ወኔው አይኖርም። ውይይት ያልተካሄደባቸው የሆቴልና ህንፃዎች አዳራሾች አሉ ከተባለ ገና ያልተሰሩት ብቻ ናቸው። በመሆኑም ችግሩ ዘመን ተሻጋሪ ነው ማለት ነው።

እንደ የአፍሪካ ቀንድ ጉዳዮች ተንታኙ አሰይድ አብዱራህማን አቡሃሺም ሙያዊ ማብራሪያ (ባለፈው ዓመት ከቢቢሲ ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደ ገለፁት)፣ ባለፉት ጥቂት ዓመታት የአፍሪካ ቀንድ አገራት እንዲሁም ምዕራባውያኑ፣ ቱጃሮቹ የአረብ አገራት፣ ቱርክ፣ ሩሲያ እና ቻይና በአካባቢው በተለያዩ መስኮች ያላቸውን የተጽእኖ ስፍራ ለመያዝ የቻሉትን ሲያደርጉ ቆይተዋል።

ግጭት እና የፀጥታ ስጋት የማይለየው የአፍሪካ ቀንድ ቀጠናዊ እና በዓለም አቀፋዊ ተጽእኖዎች እየተናጠ ነው፤ በአሁኑ ወቅት በተለያዩ ወገኖች እየተካሄዱ ያሉት ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴዎች ለዚህ ጥሩ ማሳያዎች ናቸው። በተለይ በኤርትራ፣ በኢትዮጵያ፣ በሱዳን እና በሶማሊያ በኩል የሚካሄዱ ተደጋጋሚ ቀጠናዊ ግንኙነቶች እንዲሁም የአሜሪካ፣ የቻይና እና የሩሲያ ከፍተኛ ዲፕሎማቶች እንዲሁም ባለሥልጣናት ወደ አፍሪካ ቀንድ አገራት በተደጋጋሚ መመላለሳቸውም እንደዛው።

> **በድፍን "አህጉሪቱ እየተስተዋሉ ያሉት ችግሮች ማለትም፣ የሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ የከፋ ሙስና፣ ኢ-እኩልነት፣ ድህነት፣ የጤናና ትምህርት ተደራሽነት፣ የእርስ በእርስ ግጭት ወዘተ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዴት ነው ሊቆሙ የሚገባቸው? " የሚለው ላይ መሪዎቹ አፍ ለአፍ ገጥመው ሊመክሩና ሊመካከሩ፤ ሊወስኑና ወደ ተግባርም ሊገቡ ይገባል**

ቀጣናው እንደ አሜሪካ፣ ሩሲያ እና ቻይና ካሉ ታላላቅ ኃያላን አገሮች ትኩረት ነጻ ሆኖ አያውቅም። የሩሲያ፣ የቻይና እና የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች የአፍሪካ ቀንድ አገራትን ጨምሮ በተለያዩ የአፍሪካ አገራት ውስጥ በተደጋጋሚ ጉብኝት ማድረጋቸውም የዚሁ ቀጣናውን በትኩረት የመከታተላቸው እንቅስቃሴ አካል ነው።

ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት በኋላ በአፍሪካ ውስጥ ያላት ምጣኔ ሃብታዊ፣ ፖለቲካዊ እና ወታደራዊ ተጽእኖ ሰፍቶ የቆየው አሜሪካ "በአሁኑ ወቅት በተለይ በቻይና እና በሩሲያ እየተፈተነ" መሆኑን ለጣቢያው የተናገሩት አቶ አሰይድ፤ በተለይ ባለፉት ጥቂት አስርታት ውስጥ በዓለም መድረክ ኃያልነቷ እየጎላ የመጣው ቻይና ከወታደራዊ እና ከፀጥታ ጉዳዮች በተለየ፣ የአፍሪካ አገራት በዋናነት በሚሹት የመሠረተ ልማት ግንባታ እና የምጣኔ ሃብት ልማት በኩል ትስስሯን እያጠናከረች ነው፤ ይህም ለአሜሪካ ስጋት ሆኗል።

ቻይና ምጣኔ ሃብታዊውን ትስስር ቅድሚያ ሰጥታ ትጀምረው እንጂ፤ ውሎ አድሮ ወደ ወታደራዊው መስክ መሻገሩ ስለማይቀር ለአሜሪካ ትልቅ ስጋት ነው "እንደምትሆንም፤ አሜሪካ በአፍሪካ፣ በተለይም በአፍሪካ ቀንድ እያደረገችው ያለው ከፍተኛ ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ ደግሞ እየጨመረ የመጣውን የሩሲያ እና የቻይናን ተፅዕኖ ለማክሸፍ ያለመ ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚችልም ይናገራሉ።

አፍሪካ ቀንድ አገራት ካለባቸው የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ የምጣኔ ሃብት ቀውስ፣ የጦርነት እና የፀጥታ ችግር አንጻር በተለያዩ ጊዜያት ትስስራቸውን ለማጠናከር ሲሞክሩ ይታያል። ኢጋድን የመሳሰሉ ተቋማትንም በማቋቋም ተፅእኖዎችን ለመግታት መጣራቸው የአደባባይ ሚስጥር ነው። ከወቅታዊ ተግዳሮቶቻቸው እና ፍላጎቶቻቸው አንጻር የአካባቢው አገራት የሁለትዮሽ እና ከዚያም በላይ የሆኑ ጥምረቶችን ሲመሠርቱም ታይተዋል።

"አገራቱ አንድ ላይ በመሆን በጋራ መቆም ካልቻሉ በቀጣናው እና በዓለም አቀፍ መድረክ ደካማ ይሆናሉ" የሚለውን የምሁራን አስተያየት በመረዳትም ይሁን፤ ወይም፣ ከላይ እንደ ጠቀስነው የሕብረቱ ኮሚሽን ሙሳ ፋኪ "አንድነት እና ሕብረት የግድ" መሆኑን በመገንዘብ ሁሌም መፍትሄ ያሉትን ሁሉ ከማድረግ ወደ ኋላ ብለው አያውቁም።

ከላይ የጠቀስናቸው ተመራማሪ እንደሚነግሩን ከሆነ አገራቱ ሁሌም (በጋራም፤ በግልም) ለመፍትሄ ቢፍጨረጨሩም ከተግዳሮት ሲፀዱ አይታዩም። በመሆኑም፣ የአሁኑ የሕብረቱ ኮሚሽን ሊቀመንበር ሙሳ (Moussa Faki Mahamat) ጠበቅ ያለ ንግግር አፍሪካ እንደ አህጉር ለመቀጠል ያሏት ሀብቶች ሁለት ናቸው፣ እነሱም አንድነት እና ሕብረት (Unity and Solidarity) ብለዋል።

የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት የየራሳቸው ተግዳሮት ያለባቸው ናቸው የሚሉት አሰይድ "አገራት ውስጣዊ ችግሮቻቸውን ሳይፈቱ እና ሳይጠናከሩ የሚፈጥሩት ማንኛውም ጥምረት ጊዜያዊ ካልሆነ በስተቀር ጠንካራ፣ ዘላቂ እና ውጤታማ ሊሆን አይችልም። ስለዚህም የቀጠናዊ ጥምረት ኃይል ከውስጣዊ ጥንካሬ የሚመነጭ ነው" ሲሉም ነው የሚገልፁት። "ቢሆንም ግን በአፍሪካ ቀንድ አገራት መካከል ቢያንስ ግንኙነት፤ ውይይት እና ትብብር ለመፍጠር ፍላጎት መኖሩ እንደ አንድ አዎንታዊ ነጥብ ሊወሰድ ይችላል በማለትም ተስፋቸውን ያካፍሉናል።

ጉባኤው "ይኹን እንጂ፣ የአፍሪካ ቀንድ አገራት በዲፕሎማሲ፣ በፖለቲካ እና በወታደራዊ መስኩ በተናጠል ከሚቀራረቡት ጋር ሲደጋገፉ እና አብረው ሲቆሙ ቢታዩም ጠንካራ እና ዘላቂ የትብብር ማዕቀፍ ግን ለማዳበር አልቻሉም። የሚለውን ከዓመት ዓመት የሚገላበጥ አስተያየት ከልቡ መርምሮና "ለምን?" ብሎ ለዘላቂ ሰላምና ለችግሩ መፍትሄ የሚሆን ውሳኔን ያሳልፍ ዘንድ ቀጣናው ያለበት ሁኔታ ራሱ ግድ ይላል። መሪዎቹም በዚሁ ማእቀፍ ውስጥ ሆነው ጥቂት ሊቆዝሙና ወደ ጋራ መፍትሄም ለመጡ ይገባል።

እ.ኤ.አ. በ1963፣ 32 ነፃ መንግሥታት "የአፍሪካ አንድነት ድርጅት" በማለት ያቋቋሙትና በ2002 (እ.ኤ.አ) ወደ "የአፍሪካ ሕብረት የተሸጋገረው ሕብረትና በዚሁ ሕብረት አማካኝነት የሚካሄደው ጉባኤ የአህጉሪቱ የሁሉም ነገር የስበት ማእከል እንደ መሆኑ መጠን ከቃላት ባለፈ "እውን ለአፍሪካ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሄ ባሉትና ባለሙት መሰረት እየሄደ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን መፈተሽ ግዴታ ይሆናል።


"ለአፍሪካ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሄ የሚለው መርህ መስራች እና አራማጆች፤ የአሁኖቹን፣ የአህጉሪቱ ቁልፍ ችግሮች መፍቻ ይሆናል የተባለው የፓን አፍሪካ ፓርላማ አባላት፤ እንዲሁም፣ በአህጉሪቱ የሚስተዋሉት ችግሮች ተቀርፈው የበለጸገች አፍሪካን እውን ለማድረግ የጸና አቋም ያላት ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎች የአህጉሪቱ ሀገሮችን የሚካያትት ነው። ለዚህም የፓን አፍሪካ ፓርላማ አባላትና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች የጋራ ስብሰባ እዚህ አዲስ አበባ፣ ባለፈው ህዳር ወር መካሄዱ ይታወሳል።

የአፍሪካ ሀገራት የራሳቸውን ችግሮች በራሳቸው መፍታት እና በአህጉራዊ ጉዳዮች ውስጥ የውጭ ተዋንያንን ጣልቃ ገብነትና ተጽዕኖ መቀነስ ስለ ሆነው፤ ስለ "ለአፍሪካ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሄዎች" ገፉና ሰፋ አድርጎ ለመረዳት፣ የፖለቲካ ሳይንስ ተመራማሪው ፕሮፌሰር ቴሪ ሜይስ "African Solutions for African Problems: The Changing Face of African-Mandated Peace Operations" በሚል ርዕስ ለንባብ ያበቁትን ጥልቅ ስራ ማየቱ ተገቢ ነው፤ እንዲሁም፣ የአፍሪካ ችግሮች በአፍሪካውያን እንዲፈቱ ጽኑ አቋም ካላቸው ግንባር ቀደም ሀገራት አንዷ ኢትዮጵያ መሆኗን ጠቅሶ ማለፍ ተገቢ ይሆናልና አድርገነው እንለፍ።

በድፍን "አህጉሪቱ እየተስተዋሉ ያሉት ችግሮች ማለትም፣ የሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ የከፋ ሙስና፣ ኢ-እኩልነት፣ ድህነት፣ የጤናና ትምህርት ተደራሽነት፣ የእርስ በእርስ ግጭት ወዘተ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዴት ነው ሊቆሙ የሚገባቸው?" የሚለው ላይ መሪዎቹ አፍ ለአፍ ገጥመው ሊመክሩና ሊመካከሩ፤ ሊወስኑና ወደ ተግባርም ሊገቡ ይገባል። ጉባኤው የ"አጀንዳ 2063 አፈፃፀምን በመገምገምም ቀጣይ አቅጣጫን ሊያስቀምጥ እናት አፍሪካ ብቻ ሳትሆን የተቀመጠበት ወንበር ራሱ ግድ ይለዋል።

መልካም ጉባኤ!!!

# ባለውለታዎቻችን






# የዓድዋ ፊት-አውራሪ ጀግኖች

**ክብረአብ በላቸው**

የየካቲት ወር በኢትዮጵያ ታሪክ ጉልህ ሥፍራ አለው። የኢትዮጵያውን የነፃነት ተጋድሎ ታሪክ በደምና አጥንት የተፃፈበት ወር ነው፤ ከእነዚህ አበይት የታሪክ ክስተቶች አንዱ የዓድዋ ድል ነው፡፡ የዓድዋ ድል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ክብር ማኅተም፤ የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ተጋድሎ ቀንዲል ነው፡፡ የመላው ዓለም ተፈጥሯዊ ግብር እና ሰብአዊ ክብር የታደሰው፤ በእውነት በፍትህ እና በህልውና ላይ የተቃጣው ጥቃት ድባቅ የተመታው በዓድዋ የጥቁር ህዝቦች ታላቅ ድል ነው፡፡

የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም በግሩም ሥነሥርዓት የተደራጀ ግዙፍ የኢትዮጵያ ሠራዊት የማይታሰበውን ፈጽሟል። ወራሪው የጣሊያን ኃይል ላይ ድባቅ በመምታት ድልን ተቀዳጅቷል። ስግብግብነት በተጠናወተው የአውሮፓውያን መስፋፋት፤ ኢትዮጵያ ነጻነቷን በተሳካ መልኩ አስጠብቃለች ሲሉ ያነሳሉ፤ ዝነኛው የታሪክ ፕሮፌሰር ራይሞንድ ዮናስ፦ «የዓድዋ ጦርነት፤ በዘመነ ቅርምት የአፍሪቃ ድል» በተሰኘው መጽሐፋቸው። ሃያ ዘጠኝ ሺህ ፈረሰኞችን ጨምሮ ከመቶ ሺህ እስከ መቶ ሃያ ሺህ የሚገመት አንድ ሺህ ኪሎ ሜትር በባዶ እግሩ የተጓዘ የኢትዮጵያ የገበሬ ሠራዊት፤ በወታደራዊ አካዳሚ የሠለጠነውን የአውሮፓ ወራሪ ጦር የካቲት 23 ማለዳ አሥራ አንድ ሰዓት ግድም ገጥሞ ከረፋዱ አራት ሰዓት ላይ ማሸነፉን አረጋግጧል ይለናል የታሪክ ተመራማሪው ጆርጅ በርክሌይ፡፡

የዓድዋ ጦርነትና ዳግማዊ አፄ ምኒልክ በተሰኘና ዳኘው ኃይለሥላሴ ወደ አማርኛ በተረጐሙት መጽሐፍ ላይ፤ የኢትዮጵያ ገበሬ ሠራዊት ፈረሱ ላይ ሆኖ የጋሻውን እምብርት መሬት ላይ እያጠቀሰ ጐራዴውን አየር ውስጥ እየቀዘፈ በተቆጣና በቆረጠ መንፈስ በጀግንነት ተዋግቷል። ጦርነቱ በተጀመረ ከአምስት ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሃምሳ ስድስቱም የኢጣሊያ መድፎች ሙሉ ለሙሉ ተማርከዋል፡፡ የቅኝ ገዢውን ወራሪ ሠራዊት ከመሩት ጄኔራሎች ጄኔራል አልቤርቶኒ ሲማረክ የሠራዊቱ ዋና አዛዥ ጄኔራል ባራቴሪ ከጥቂት አጃቢዎቹና በሽንፈት ከተበታተኑ የጣሊያን ወታደሮች ጋር ሸሽቷል፡፡

በዚህ ድብልቅልቅ ያለ ውጊያ ከሃምሳ ስድስቱ የጣሊያን መድፎች በተጨማሪ ብዙ ሺህ ቀላልና ከባድ መትረየሶች እንዲሁም የነፍስ ወከፍ ጠመንጃዎች በአሥር ሺዎችና በመቶ ሺዎች ከሚቆጠሩ መሰል ጥይቶቻቸው ጋር ተማርከዋል፡፡ በአጠቃላይ ምርኮው ወደ አዲስ አበባ የተጓጓዘው በአምስት መቶ አጋስሶች ተጭኖ ነው፡፡ ታላቁ የጥቁር ሕዝቦች ድል የዓድዋ ድል በመላው ዓለም ፖለቲካ ላይ ከፍተኛና ዋነኛ ለውጦች አምጥቷል፡፡

የእንግሊዝ ጋዜጦች በዓድዋ ድል ማግስት የዓለም ታሪክ ተገለበጠ ታላቅ የትውልድ ኃይል በአፍሪካ ተቀሰቀሰ … ብለው ፃፉ፡፡ ዘመናዊት ኢትዮጵያን የፈጠሩ የተባሉት ዳግማዊ አፄ ምኒልክ በሌሉበት እና በአካል ባልተገኙበት የነፃነት ተጋድሎ መሪዎች ጉባኤ የአፍሪካ ብሎም የመላው ዓለም ጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ተጋድሎ መሪ ተደርገው ተመርጠዋል።

በዚህ ለነፃነት፣ ለፍትህና ለእኩልነት በተደረገው ተጋድሎ በግንባር ቀደምትነት የሚነሱ 12 የጦር መሪዎች አሉ። የእነዚህ የሀገር ባለውለታ አባቶች ገድል በዚህ ፅሑፍ እናስነብባችኋለን።

በመጀመሪያ የምናገኛቸው ፊት አውራሪ ገበያው ገቦ ጉርሙ ወይም በጀግንነት ስማቸው አባ ጎረው ናቸው። እኚህ ሰው ከአድዋ ጦርነት አስቀድሞ ከነበረው ከአምባለጌ ጦርነት ጀምሮ ለሀገራቸው ነፃነት ትልቅ ተጋድሎ ያደረጉ አዋጊና ተዋጊ ሰው ናቸው። በመድፍ ተኳሽነታቸው የሚታወቁት ፊት አውራሪ ገበያው ከጠላት ጋር በጀግንነት ሲዋጉ ቆይታው በጦርነቱ የመጨረሻ ቀን በክብር ተሰውተዋል።

ሌለኛው የዓድዋ ጀግና ልዑል ራስ መኮንን ወልደሚካኤል ጉዲሳ ናቸው። በጀግንነት ስማቸው ደግሞ አባ ቀኘው። እኚህ ጀግናም ከአምበላጌ ጦርነት ጀምሮ እስከ ዓድዋ ጦረኛ በማዝመት ፈረሰኛና እግረኛ በመምራት ተዋጊቶ በማዋጋት ለሀገራቸው ሉዓላዊነት ትልቅ ጀብዱ የፈፀሙ ሰው ናቸው። እኚህ ሰው ከዚህ በተጨማሪ ወራሪው ጣልያን የውጫሌን ውል አስታኮ ኢትዮጵያን ለመውረር ስመጣ ጉዳዩን በሰላም እልባት እንዲያገኝ ለማድረግ ከፍተኛ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ያደረጉ ሰው ናቸው። ጦርነቱ አይቀሬ ሲሆን ግን በጀግንነት ተፋልመው ሀገራቸውን ከወራሪ ታድገዋል።

በሦስተኛነት የምናነሳቸው ደግሞ ንጉሥ ተክለሃይማኖት ተሰማ ጎሹ ናቸው። በጀግንነት ስማቸው ደግሞ አባ ጠና ይሰኛሉ። ንጉሥ ተክለሃይማኖት ከአድዋ ጦርነት አስቀድሞ በነበሩ በተለያዩ ዓውደ ውጊያዎች ተሳትፎ አድርገዋል። በዓድዋ ጦርነት ደግሞ ፈረሰኛን ከእግረኛ አዋህደው በመምራት ጠላትን በጀግንነት ተፋልመው ያርበደበዱ ለሀገራቸው ነፃነት መስዋዕትነት የከፈሉ ጀግና ናቸው።

ሌለኛው ሰው ደግሞ ንጉሥ ሚካኤል አሊ ልበን ናቸው። የጀግንነት ስማቸው ደግሞ አባ ሻንቆ ይሰኛል። እኚህም ሰው በተመሳሳይ ከዓድዋ ጦርነት ባሸገር በተለያዩ አውደ ውጊያዎች ማለትም በመቀሌ፣ በአምባለጌ ጦርነቶች እግረኛና ፈረሰኛ ጦር ድንቅ በሆነ ሁኔታ በመምራት ለሀገራቸው ውድ ዋጋ የከፈሉ ጀግና ኢትዮጵያዊ ናቸው።

በአምስተኛ ደረጃ ላይ የምንመለከታቸው ደግሞ ደጃዝማች ባልቻ ሳፎ ሮባ ናቸው። አባ ነፍሶ በተሰኘው የፈረስ ስማቸው የሚታወቁት እኚህ ጀግና የንጉሥ ምንልክ የግምጃ ቤት በጅሮንድም ነበሩ። እኚህ ጀግና ሰው በተመሳሳይ በመቀሌና በዓድዋ ጦርነቶች እግረኛና ፈረሰኛ ጦር በመምራት ለሀገራቸው በጀግንነት የተፋለሙ ሰው ናቸው። “ገበያው ቢሞት ተተካ ባልቻ መድፍ አገላባጭ ብቻ ለብቻ” ተብሎ የተገጠመላቸው ደጃዝማች ባልቻ በዓድዋ ጦርነት ሽንፈት ተከናንቦ የተመለሰው የጣሊያን ጦር ኢትዮጵያን ከዓመታት በኋላ ደግሞ ስወረት በወቅቱ ከንጉሥ ኃይለሥላሴ ጋር ስምምነት ባይኖራቸውም ከራሳቸው ጉዳይ ሀገራቸውን በማስቀደም ደግሞ በጀግንነት ተፋልመው የተሰው ጀግና ናቸው።

ራስ ወሌ ብጡል ኃይለማርያም ደግሞ ሌላኛው ሰው ናቸው። በጀግንነት ወይም በፈረስ ስማቸው አባ ጠጣው የሚሰኙት እኚህ ሰው ጀግና ጦረኛ እንደነበሩ ይነገርላቸዋል። እንደ ሌሎች የኢትዮጵያ ጀግኖች ሁሉ ጦራቸውን ከአምበላጌ እስከ ዓድዋ ዘምተውና አዝምተው ለሀገራቸውና ሕዝባቸው ሉዓላዊነትና ነፃነት ትልቅ ዋጋ የከፈሉ ጀግና ናቸው። ራስ ወሌ የእቴጌ ጣይቱ ወንድም ሲሆኑ፤ ደጀኑን ጦር ከደብረ ታቦር ተነስተው እየመሩ በቅድሚያ የዘመቱት በአምባላጌ ግንባር ነበር።

በሰባተኛ ላይ የምናነሳቸው ጀግና ደግሞ ፊት አውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ ሁንዱል ናቸው። አባ መቻል በተሰኘው የጀግንነት ስማቸው የሚታወቁት እኚህ ሰው በጦር አማካሪነታቸውም ይታወሳሉ። እኚህ ሰው ፊት አውራሪ ገበያው በጦር ሜዳ በጀግንነት ስሰው የሳቸውን ቦታ ተረክበው ጦር በማዝመት ድል የተቀዳጁ ጀግና ናቸው። በፈረስም በእግርም ተዋግተውና አዋግተው ለሀገር ነፃነት የተዋደቁ ሰው ናቸው።

ፊት አውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ በጦረኝነታቸው ወደር ከሌላቸው ውድ ኢትዮጵያዊ ጀግኖች መካከል አንዱ ናቸው። በዓድዋ የጦርነት ውሎ በርከት ያለ ሠራዊት ይዘው ጉልህ የጀግንነት ተጋድሎ አድርገዋል። እኚህን ሰው በፍርድ አዋቂነታቸው ስማቸውም ሀብቴ አባ መላ ይሉዋቸዋል። አባ መላ አጼ ምኒልክ ካረፉ በኋላ የስልጣን ሽኩቻ እንዳይነሳ በማለት ሀገሪቷን በማረጋጋት ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

ራስ አሉላ እንግዳ ቁቢ ሌላኛው የዚህ ታሪክ አካል ጀግና ናቸው። በጀግንነት ስማቸው አባ ነጋ ይሰኛሉ። በስለላ ታሪካቸው የሚታወቁት እኚህ ሰው በተለይ የጣሊያን ጦር አሰላለፍ ምን ይመስላል የሚለውን በደንብ በመረዳት የኢትዮጵያ ጦር የተሻለ ቦታ ይዞ እንዲጠብቅና በወራሪው የጣሊያን ጦር ላይ ከፍተኛ ኪሳራ እንዲያደርስ ጉልህ አስተዋጽኦ የነበራቸው ሰው ናቸው። ተዋግተውና አዋግተውም በጦር ሜዳ ጀብዱ የፈፀሙ የጦር መሪ ናቸው።

ሌለኛው ጀግና ደግሞ ራስ መንገሻ ዮሐንስ ምርጫ ናቸው። በጀግንነት ስማቸው አባ ግጠም ይሰኛሉ። እኚህ ሰው ከአድዋ አስቀድሞ በነበሩ አውደ ውጊያዎች የተሳተፉ ናቸው። በተለይ በሁናትና ሰናፍ ግምባር ትልቅ ታሪክ የሰሩ ሰው ናቸው። በዓድዋ ጦርነትም በመሪነት ተሳትፈው የተዋደቁና ለሀገራቸው ትልቅ ዋጋ የከፈሉ ጀግና ሰው ናቸው።

ታሪክ በደማቅ ቀለም ከትቦ ካስቀመጣቸው የጦር መሪዎች መካከል ዋቅሹም ጓንጉል ብሩ ገብረመድህን አንዱ ናቸው። በጀግንነት ስማቸው አባ መርከብ ይሰኛሉ። እኚህ ጀግና በተለያዩ አውደ ውጊያዎች የተፋለሙ ሰው ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ የወራሪውን የጣሊያን ጦር መሪ ጄኔራል አልቤርቶኒን ጨምሮ ሌሎች የጠላት ጦር አባላትን በመማረክ ለአድዋ ድል ጉልህ አስተዋጽኦ የነበረቸው የጦር መሪ ናቸው።

ራስ አባተ ቧያለው ንጉሡ ሌለኛው የአድዋ ጀግና የጦር መሪ ናቸው። በጀግንነት ስማቸው አባ ይትረፍ ይሰኛሉ። የልቀ መኳንነት ማዕረግ የነበረችው እኚህ ሰው በመድፍ ተኳሽነተቸው የሚታወቀውና በተለያዩ አውደ ውጊያዎች ትልቅ ተገድሎ የደረጉ የኢትዮጵያ ጀግና ናቸው። እዚህ ላይ አንድ ትለቅ ገድል እናነሳለን እሱም ከዓድዋ በፊት የመቀሌውን ስትራቴጅካዊ የውሃ ምንጭ የመያዝ የራስ አባተ ቧ ያለው እና የደጃዝማች ባልቻ አባ ሳፎን ጀብዱ።

አፄ ምኒልክ ጦራቸው መቀሌ ደርሶ ሰፈሩን ተከፋፍሎ ከያዘ በኋላ በጣልያን ምሽጉ ዙሪያ ራቅ እያለ ሰፈረ። ድንኳን በሚተከልበትና ጭነት በሚራገፍበት ጊዜ አንድ በቅሎ ፈርጥጦ ወደ ጣልያኖች ምሽግ ሮጠ። አንድ ሰው ሊመልሰው ሲሮጥ ባዩ ጊዜ ጣልያኖቹ የመድፍ ተኩስ ጀመሩ። ጣልያኖቹ አብዝተው መተኮሳቸውን ንጉሰ ነገስቱ በተመለከቱ ጊዜ ሊቀ መኳስ (በኋላ ራስ) አባተ ቧ ያለውን እና በጅሮንድ (በኋላ ደጅአዝማች) ባልቻ አባ ሳፎን ሂዱ እናንተም ተኩሱባቸው ብለው አዘዙ እና የምሽቱ ጊዜ በመድፍ ተኩስ አለፈ። ወደ ማታ ንጉሱ እንደገና ሊቀ መኩስ አባተን እና በጅሮንድ ባልቻን ጠርተው “እነዚህን ጣልያኖች ከጉድጓዳቸው ሳላስወጣ የትም አልሄድም እናንተም የጠላት መድፍ ጥይት የማይደርስበትን ስፍራ መርጣችሁ ከዚያ ሆናችሁ ምሽጉን በመድፍ ምቱት” ብለው አዘዟቸው።

ሊቀ መኳስ አባተ ጦራቸውን ይዘው በምሽጉ በስተግራ የጣልያኖችን ቃፊር ጠባቂ አባርረው ምሽግ አበጅተው መድፍና መትረየሳቸውን እንደጠመዱ በጅሮንድ ባልቻም በስተቀኝ በኩል ሌሊቱን ምሽግ ሰርተው መድፍ እና መትረየሳቸውን ጠመዱ። ጣልያኖችም የእነሱን መጠጋት ባወቁ ጊዜ የመድፍ እና የጠመንጃ ተኩስ አበረከቱ። አነጣጥሮ በመተኮስ የተመሰገኑት ሊቀ መኳስ አባተም በሩቅ በሚያሳየው መነጸራቸው ጣልያኖች ታቦቱን አስወጥተው መድፍ በመትከል የመሸጉበትን ቤተክርስትያን ህንፃ በመመልከታቸው አስተካክለው ቢተኩሱ የመድፉ ጥይት በቤተክርስቲያኑ መስኮት ገብቶ የጠላትን መድፍ እግር ሰባበረው። ጣልያኖችም ከተበላሸው መድፋቸው ጭስ እየጨሰ ባዩ ጊዜ በአፀፋው የመድፍ ጥይት ሊቀመኳስ አባተን እና በጅሮንድ ባልቻ ባሉበት ቦታ ላይ እንደ በረዶ አወረዱባቸው። ነገር ግን አንድም ሰው አልቆሰለም። ይህን ውጊያም አፄ ምኒልክ፣ ንጉስ ተክለ ሃይማኖት እና ሌሎችም መኳንንቶች ከድንኳናቸው ወደላይ ካለው ከፍተኛ ስፍራ ላይ ሆነው በመነፅር ይመለከቱ እንደነበር ታሪክ ያስረዳል።

ራስ ቢትወደድ መንገሻ አቲከም ቢተርፉ ሌላኛው የጥቁር ሕዝቦች ሁሉ ድል የሆነው አድዋ ጦርነት ተሳተፊ የጦር መሪ ናቸው። በጀግንነት ስማቸው አባ ገድብ ይሰኛሉ። በንጉሥ ምኒልክ ይወደዱ የነበሩት እኚህ ሰው የራስ ቢትወደድነት ማዕረግ ያገኙት በጦር ምክራቸው የታወቁ ስለነበር ነው። በዓድዋ ጦርነት እግረኛና ፈረሰኛ አዝምታው ትልቅ ድል የተቀዳጁት እኚህ የጦር ጀግና ከጦርነቱ በኋላም ድሉን ተከትሎ በተካሄደውና አንድ ኢትዮጵያ በፀነችበትን የውጫሌ ውል ደግሞ ውድቅ በሆነበት የአዲስ አበባው ስምምነትና የሰላም ድርድር የተከፈሉ ሰው ናቸው።

የዓድዋ ድል ኢትዮጵያውያን ከጥግ እስከ ጥግ ቀፎው እንደተነካበት ንብ ተምመው በአንድ ጥላ ስር እንዲሰባሰቡ ያደረገ ታሪካዊ ክስተት በመሆኑ የኢትዮጵያውያንን ትብብር እና አንድነት ከማሳየቱም በላይ ለመላው የጥቁር ህዝብ የነፃነት ምልክት መሆናችንን ማሳያ ነው።

ከኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ባለፈ የአፍሪካውያን ብሎም ጥቁር ሕዝቦች ሁሉ ድል የሆነው ዓድዋ የተገኘው እንደ ድር አብረው ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ነፃነት በተዋደቁ በእነዚህ ፊት አውራሪ የጦር ጀግኖች ነውና ዛሬ ላይ ለእነዚህ አባቶቻችን ክብር እጅ እንነሳለን።

# ስፖርት

## ወደ ዱባይ ያቀናው የሸገር ደርቢ

ዓለማየሁ ግዛው

ሁለቱን የአዲስ አበባ ታላላቅ ክለቦች የሚያገናኘው የሸገር ደርቢ ጨዋታ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሀገር ውጪ በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች ዱባይ ይካሄዳል። ጨዋታው ከሀገር ውጪ ሲካሄድ ክለቦቹ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን እንዲቀስሙና ከባህር ማዶ ደጋፊዎቻቸው ጋር እንዲገናኙ እንዲሁም ገቢ እንዲሰበስቡ ታስቦ እንደሆነ ተጠቁሟል። ጨዋታው መጋቢት 17 በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች እንደሚካሄድ አዘጋጆቹና ሁለቱ ክለቦች ከትናንት በስቲያ በጋራ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ አስታውቀዋል።



ጨዋታው መጋቢት 17 በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች እንደሚካሄድ በመግለጫው ተጠቁማል፣

ጨዋታውን ከሀገር ውጪ ለማካሄድ በርካታ ምክንያቶች እንዳሉ የተጠቀሰ ሲሆን፣ ክለቦቹ የሀገሪቱ ታላላቅና የበርካታ ደጋፊ ባለቤት መሆናቸው ጨዋታውን ባዘጋጁት አካላት ቅድሚያ ተሰጥቶ ዓለም አቀፍ ተሞክሮ እንድያገኙ እንዳስመረጣቸው ተገልጿል።

የፊፋ የጨዋታ አዘጋጅ አቶ ፍጹም አድዕኖ ከመጋቢት 14-17 በዱባይ በተዘጋጀው መርሃግብር የሁለቱን ክለቦች የወዳጅነት ጨዋታ ጨምሮ የተለያዩ ሁነቶች መሰናዳታቸውን ተናግረዋል፡፡ የጨዋታውን ዋና አላማ ሲያስረዱም የኢትዮጵያ ክለቦች ዓለም አቀፍ ተሞክሮ እንዲያገኙና የተባበሩት ዓረብ ኤምሬቶችና የኢትዮጵያን እግር ካስ ግንኙነት ለማጠናከር መሆኑን ገልፀዋል። ይህ የመጀመርያ እንጂ የመጨረሻ እንዳልሆነ ጠቁመውም፣ ለኢትዮጵያ ቡናና ቅዱስ ጊዮርጊስ የተሰጠው ባለቸዉ የደጋፊ ብዛት፣ እርስ በርስ ባለዉ ፉክክር እንዲሁም ስምና ዝናቸው መሆኑን አብራርተዋል።

ክለቦቹ በዳባይ በሚኖራቸው ቆይታ ከተለያዩ ሀገራት ክለቦች ጋር የልምድ ልዉዉጥ የሚያደርጉ ሲሆን የራሺያውን ክለብ ሎኮሞቲቭ ሞስኮን ጨምሮ የሌሎች ሁለት ሀገራት ክለቦች እንደሚገኙበት ተገልፃል፡፡ ከእነዚህ ክለቦች ጋር የጊዜ ማጣር በማጋጠሙ እንጂ የወዳጅነት ጨዋታም ለማድረግ ታስቦ እንደነበር ተጠቁሟል። ፈረሰኞቹና ቡናማዎች ወደ ዱባይ ሲያቀኑ በከተማዋ የሚገኙና ከተለያዩ የአረብ ኤምሬቶች የተወጣጡ የሁለቱም ክለቦች ደጋፊዎች አቀባበል የሚያደርጉላቸዉ ይሆናል።

በሚዘጋጅ የእራት ግብዣ ላይ የገቢ ማሰባሰብ መርሀ ግብር እንደሚኖር የተጠቆመ ሲሆን፣ በዚህም የጊዮርጊስና የቡና የቀድሞ ታዋቂ ተጫዋቾች ማለያዎች ለጨረታ ይቀርባሉ። ጨረታው የተዘጋጀው የሁለቱም ክለቦች ደጋፊዎች የራሳቸው የሆነ ጥሩ ጊዜ ኖሮአቸው ከክለባቸዉ ጋር እንዲያሳልፉ ታስቦ እንደሆነ ተጠቅሷል። ይህም የዳያስፖራዉ ማህበረሰብ የናፈቀዉን ደርቢ በቅርቡ አግኝቶ የመመልከት እድል እንዲኖረው ያደርጋል ተብላል።

ሁለቱ ክለቦች በቦለርስ አካዳሚ ልምምዳቸዉን በሚያደርጉበት እለት የክለቦቹ አመራርሮች የሚሳተፉበት ሴሚናር እንደሚኖር ታውቋል። ይህም ለክለቦቹ የአካዳሚ ግንባታ ማማከርና አጋርነትን ለመፍጠር ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡

ወደ ስፍራው አቅንተው በስቴድየም የሁለቱን ክለቦች የደርቢ ጨዋታ የመመልከት ዕድል ለማይኖራቸዉ ደጋፊዎች ከተባባሪ የሀገር ዉስጥ የሚድያ ተቋም ጋር በመሆን የቀጥታ የቴሌቪዥን ስርጭት እንደሚኖርም ተጠቁሟል።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ስፖርት ክለብ ሥራ አስኪያጅ አቶ ሰለሞን በቀለ፣ የማህበሩ ቦርድ ሁኔታውን በሚገባ እንደተመለከተና በክለቡ ስም አዘጋጁን አመስግኖ የፕሮግራሙ መዘጋጀት የክለቡንና የሀገርን ግንኙነት በማጠናከር ፋይዳዉ ብዙ መሆኑን ጠቀሰዋል። የፕሪሚየር ሊግ የመጀመሪያ ዙር ጨዋታዎች ተጠናቀው ሁለተኛ ዙር የሚጀምርበት ወቅት በመሆኑ ለክለቡ ትልቅ ተሞክሮ እንደሚፈጥርም ተናግረዋል። ይሄም በዱባይ የሚገኙ የቀድሞ ደጋፊዎችን ለማግኘትና አዳዲስ ደጋፊዎችን ለማፍራት የፕሮግራሙ መዘጋጀት መልካም አጋጣሚ በመሆኑ የክለቡን ማልያዎችና ሌሎች ቁሳቁሶችን በማጓጓዝ ለማቅረብም ታስቦ እየተሰራ ነው። የሁለቱ ክለቦች የደርቢ ጨዋታዎች ለሶስት ዓመታት በአዲስ አበባ ባለመካሄዳቸው ክለቦቹ ብዙ ተግዳራቶችን ማሳለፋቸውን ያስታወሱት አቶ ሰለሞን፣ ይሄን እንደመንደርደርያ በመጠቀም ወደፊት የሚፈጠሩ ዕድሎችን ለማመቻት ብርቱ ጥረት እንደሚደረግ ጠቅሰዋል።

የኢትዮጵያ ቡና ሥራ አስኪያጅ አቶ ገዛኸኝ ወልዴ፣ የሁለቱ ክለቦች ደጋፊ ለሶስት ዓመት በአዲስ አበባ ላይ መመልከት እንዳልቻሉ ገልጸው፣ ከቦለርስ አካዳሚ ጋር በዙም ውይይት እንደተካሄደና በአካል በአካዳሚና ስቴድየም ግንባታ የልምድ ልውውጥና የማማከር ዕድል እንደሚኖርም ጠቁመዋል።

በደጋፊዎች ዘንድ ሁሌም በጉጉት የሚጠበቀው የሸገር ደርቢ ጨዋታ የአዲስ አበባ ስቴድየም እድሳት ባለመጠናቁ ባለፉት ሶስት ዓመታት በላይ በመዲናዋ መካሄድ አልቻለም፡፡ በዚህም ደጋፊው በለመደው ከተማ ተናፋቂውን የደርቢ ጨዋታ መመልከት ካለመቻሉ ባሻገር ክለቦቹም ከስቴድየም የሚያገኙት ገቢ ቀርቶባቸዋል፡፡